# እናፍርበ

3ተኛ ዕትም



Scanned by CamScanner

# መክስተ ቅኔያት


እኔ ....................................................21
ልዩነት ....................................................22
የተፈታ ትዳር ....................................................23
ቅድመ ፍልስፍና ....................................................24
ኑ… ግድግዳ እናፍርስ ....................................................25
አባይ ፩ ....................................................30
ሰባት ወይም አምስት ....................................................31
መሰንቆና-ብቸኝነት ....................................................33
ሠለስቱ ምስጢራት ....................................................34
እብደት ....................................................35
ግራጫ ቀለሞች.... ....................................................36
ፍቅር ምን መሰለሽ? ....................................................40
ተስፋ ....................................................41
በክፍተቱ መሃል ....................................................42
የሰባቶች አባት ....................................................43
የምንሻው ጆሮ ....................................................46
የአንድ ካፍቴርያ ረዥም ትዝታ ....................................................47
የፍለጋ ህመም ....................................................52
የድሆች መጽናኛ ....................................................53
ሙዚቃው ....................................................54
ጊዜ ....................................................57
እምነት ክህደት እውነት ....................................................58
ትዝታ ....................................................59
ብቸኝነት ....................................................61
ወቅቶች ....................................................66
አንድ ሰው ....................................................67
ፍለጋ ....................................................68


Scanned by CamScanner

............81
የመሸነፍ ድሎች ............83
የፈረሱ መልኮች ............84
ሁለት ፍቅር ............89
ለእናንተ ............91
ሁለንተናዊነት ............93
ጸሎተ ቶማስ ............94
የጀሮ ህመሜ መነሻው ምክንያት ............95
ያልተፈጠረ ሞት ............101
ያፈር ዕንባ ጊሜ ............102
የራሱ ዓለም ሰው ............103
ሃሳብ ............105
ቡና ጣእም ናፍቆት ............106
ምናባዊ ክንፎች ............109
ዜሮ ሲደመር ዜሮ ............110
መሃል ............111
ሌሊት መሰል ዝምታ ............114
የሁለት ዘላለሞች ስጦታ ............116
መክሊትና ፍቅር ............117
በሌላኛው በኩል ............121
አፋቃሪው ፍቅር ............123
አባይ ፪ ............124

Scanned by CamScanner

ኤልያስ አሰፋ (የሙዚቃ ባለሙያ) ፣ ዮሃንስ ግዛው ፣ አንዋር አህመድ ፣ ጥላሁን አበበ (ገጣሚ) !!!

ሄለን ሃ/ጊዮርጊስ እና ማህሌት ሃ/ጊዮርጊስ...ስለ ታላቁ ትዕግስታችሁ (የእጅ ጽሁፌ ፊርማ መሰል ነውና) ምስጋናዬ ከፍቅር ጋር በፊታችሁ ትሁን...!!!

ሰለሞን ሳህለ....አዳዲስ ግጥሞችህን በሌሊት ደውለህ እንቅልፌን ማሳደድህ እንዳለ ሆኖ...የዚህን መጽሃፍ የፊደል እርማት ውለታህስ.... ይሄው...አክብሮቴ በኣይኖችህ ፊት እዚህ ገጽ ላይ...!!!

ስንታየሁ ምሕረቴ...ለሕልሞቼ ጥግ መድረስ አንተ ያልነበርክበት ጊዜ ምንም ነው...ለመልካም ማንነትህና ለታላላቅ ሕልሞችህ ስኬት...የያኒ እና የመልካም ዓምላክ ዘወትር በቀኝህ ይሁን...በክፉና በደግ ከጎንህ ያለችው ሳምራዊትስ ብትሆን እንደምን ትዘነጋለች...አክብሮቴ ይድረሳት...!!!

መሰረት ፍቅሩ እጅግ ቀና እና መልካም ለሆነው አብሮነትሽ ከነፍስ የሆነ ምስጋናዬን ይኸው እዚህ ብራና ላይ...!!!

Scanned by CamScanner

## ክቡራንን ስለማክበር ፡—

የገጣሚና ደራሲ ኤፍሬም ሥዩም እናት እመቤት ማሜ አግደው...እዚህ መጽሐፍ ላይ ሥምሽን ልዘክር እወዳለሁ...ወደ ፊትም እንዲሁ እኔን ለዚህ አይነት የጥበብ ማንነት የሰራሽኝ አንች ነሽና....ልላው ቢቀር በልጅነት ዘመኔእንጉርጉሮ ሳይሆን

"ሮሚዮ ሮሚዮ የልቤ ወለላ
ስምህን ቀይረው እባክህ በሌላ.." እያልሽ የተረከሽልኝ እንዴት ልዘነጋ እችላለሁ...በፍጹም

አብደላ ዕዝራ ከአየር ቀጥሎ ግጥም (ጥበብ) የምትተነፍሰው አንተ ነህ ይህ እስትንፋስህም ከነባር (አንጋፋ) እስከ ዘመነኛ ገጣሚያን ህይወትነቱ አሻራው ይታያል ከነዚህ መካከል አንዱ እኔ በመሆኔ ራሴን እንደ እድለኛ እቆጥረዋለው ስለ ታላቅ ስብእና ብዙ ከማለት ይልቅ ያቺ ከሁሉም ለይታ ያመመችህና እንቅልፍ የነሳችህን ግጥም የመታሰቢያ ስጦታ ላንተ ትሆን ዘንድ ጎንበስ አልኩ *(የማርያም ንግስ ዕለት)*

እናንተ ማንነቴ ላይ ብሩህ ከዋክብቶች ናችሁ።...ብርሐነ ሙሉ ሰማዩ ያለ ከዋክብት ምንም ነው ከዋክብቱም ያለ ብርሐን ብትን ጠጠሮች ናቸው ገጣሚው ማለዳ ላይ ከእንቅልፉ ሲነቃ ፊቱ በፈገግታ የሚታሸው እናንተን ሲያስብ ነው እናንተ ማለትም... ወንድም ስንታየሁ ምህረቴ ፤መሐመድ ካሳ ፤ሙሉቀን አስራት ፤ ደምሰው ኃይለሚካኤል (ጋዜጠኛ ዘሸገር) ፤ ፍሎረንስ አሰበ ፤ ኪዳኔ፤ ደምሰው መርሻ (ገጣሚ) ፤ ፍሬዘር አድማሱ (ገጣሚ) ፤ ሀብታሙ ማሞ (ገጣሚና ፊልም ዳይሬክተር) ፤ ዮሃንስ ሃብተማርያም (ገጣሚ) ፤ ምልእቲ ኪሮስ (ገጣሚ) ፤ ፋሲል ረታ ፤ ህዝቅኤል ሰብስቤ ፤ ጌቱ ግርማ ፤ ደረጀ ፍቅሩ (የፊልም ዳይሬክተር) ፤

Scanned by CamScanner

## ሃሎታ ኣባብ

አብደላ ዕዝራ

ግጥም እንደነገሩ ከዛለ ለመወሳሰብ ትንፋሽ ያጥረዋል፤ ቋንቋዉ ወርዝቶ ምናባችንን ከነጠቀ፥ እዉስጣችን ይናኛል:: ይህ ስብስብ ሳይታተም፥ ኤፍሬም እንድጓዝበት አረንጓዴዉን ሲያበራ፥ ዘዉትር ለብርቅ ቅኔ እነዝራለሁና ተስገበገብኩ:: ቆይቶ ነዉ፥ አንድ ተናዳፊ ግጥሙ መንፈሴን አዉኮ የወትሮዉ ዕዝራ መሆን የነፈገኝ:: “የማርያም ንግስ ዕለት” በሁለት ገጾች አድብቶ፥ የሰዉን ጎላዊ እየቧጠጠ ልቦናንና ሰብአዊነት ይቃትታሉ:: ይህ ግጥም ለአንድ ሳምንት ያህል ከሌላዉ አግልሎ መንፈሴን አንገላታዉ፤ ብዙ አንብቢያለሁ፤መፍካትም መጠዉለግም ተፈራርቀዋል:: ግን ለቀናት ድንዝዤ በሰዉ ጉዳይ ስብሰከሰክ፥ ለመጽሐፍ፥ ለእንስት ገላ እና ለሙዚቃ በመቀዘዝ ዝምታ ያስነከሰኝ ብቸኛ ቅኔ ነዉ:: *(ስርየት ቢሆነኝ ከዚህ ግጥም ለመመንጨቅ በነጠላ ሂሳዊ ንባብ ማንጋት አስፈለገኝ፤ መዉጫዉ ላይ ተካቷል::)* ኤፍሬም በድምፅና በወረቀት ግጥሞቹ ተደራሲን ለመመሰጥ፥ ብሎም ከአዕምሮ የሚንገዋለሉ ምስሎችና ጥያቄዎች ለመግራት አቅም አለዉና እልፍ ተከታዮች መመልመሉ አይደንቅም::

ከቀን  
በአንዱ ቀን ?  
ተቀማጭ ገጣሚ፥  
‘እስኪ ግጥም ልጻፍ’ ብሎ ተቀመጠ።  
ተቅበጠበጠ  
ተቁነጠነጠ  
ሰፋ  
ብዙ ሰፋ  
ቃላቶች ጨለሙ፥ ህሊና አንቀላፋ።  
[ገፅ 95]



Scanned by CamScanner

የሚዳሰስ ምርጊት ብቻ ሳይሆን ሥነልቦናዊ የትዉልድ ብሶትና እልልታ ሸሽጓል ግድግዳዉ:: እዉቁ ሳይንቲስት አይሳክ ኒዉተን አጭር ጥቅስ አለዉ:: *"We build too many walls and not enough bridges."* ኤፍሬም ከቀዳሚ አባቶች የተረከብነዉ ጣራና ግድግዳ በፍቅርም በጥበብም ድልድይ ጭምር መወከሉን ተቀኘበት::

ስለተላመድነዉ አካባቢ ሆነ እሳቦት ባለቅኔ ከዓፊ አዲስነት፥ ትኩስነት እዉስጡ ተምዘግዝጎ ከነደፈን፥ ከመሰጠን ግጥም እያነበብን ነዉ:: ዘይቤና ዜማዉ የምናባችንን ድንበር ተሻግረዉ የሆነ አግራሞት፥ ትካዜና ጥያቄ ያረባሉ::

እሁድ ማለዳ ሳይ
ገላዋን ታጠበች፥
ልብሶቿን ለበሰች
ሽቶ ተርከፍክፋ ከጉዳና ወጣች።
በመንገድ ስትጓዝ
የፀጉሯን መዘናፈል፥ የጡቷን መኮፈስ
የረጨችዉ ሽቶ ካደባባይ ሲነፍስ
እሷን ያየ ሁሉ ወንዱ ተጨነቀ
በደም በዉበቷ እየተደነቀ
ያስተዋሳት ሁሉ ዐይኑ መንገድ ሣተ
ከዳሌ ከጡቷ ሔደ ተከተተ።
ከቦታዉ ደረሰች።
[ገፅ 67]

ኤፍሬም ሥዩም በአመዛኙ እንቅስቃሴ ዉስጥ ነዉ ግጥም የሚያስግረዉ:: መንገድ ላይ ተባዕት በመደዳ በሴት መዓዛ ተደናግሮ ለፍትወት ሲያቃስት፥ እሷ የተዋበችዉ ለአንድ ወንድ ብቻ በመሆኑ ጉጉታቸዉ አላሸማቀቃትም:: ማፍቀር ለሌላዉ ልብን ደፍኖ፥ ለአንድ ግለሰብ መቅበጥበጥ ብቻ ሣይሆን፥ ሥነልቦናዊና ማኅበራዊ ጦሱ እዉስጣችን የሚመረቅዝ አስቀያሚነት ሊያወርሰን ይችላል:: ሌላዉ ተባዕት እንደ ታማኝ



Scanned by CamScanner

አንድ ግድግዳ ስሉ፥ ደግሞም አንድ ጣራ
ሸበታም ያቀፈ፥ ህፃናት ያዘሉ፥ ታሪክ የሚያወራ።
እናቶች እህቶች ከዝናብ ያስጠለለ
ጉልማሶች ወንድሞች ፀሃይ የከለለ
የሁለት ስባወራ፥ አንድ ግድግዳ ስሉ።
[ገፅ 25]

በአንፃሩ ረዘም ባለ በዚህ ግጥም ባለቅኔዉ የግለሰቦች ፍቅርና ፍትጊያ፥ የማኅበረሰብ ኩርፊያና ፈገግታ የቀነበበበት ብቻ ሳይሆን፥ ግድግዳ እንደ ገመና ሸፋኝ፥ እንደ የአብሮ መኖር ግለት ወካይ ሆኖ ተቅርጿል:: የበአሉ ግርማ ገፀባህሪ አበራ ወርቁ እናቱን ለመጠየቅ ከአደገበት ሰፈር ሲሄድ፥ ቤቶች ተደጋግፈዉ እንደ ሰዉ መቆማቸዉ ገርሞታል:: *“ጥንት በየሰፈሩ የነበሩ ቤቶች ተራርቀዉ የቆሙ ነበሩ:: እያንዳንዱ ቤት የራሱ የሆነ ትምክህትና ኩራት ነበረዉ:: አሁን ግን እንደ ሰንሰለት ተያይዘዋል:: ያንዱ ቤት ግድግዳ ለሌላዉ ድጋፍ ሊሆን ... ለክፉም ሆነ ለደግ በችግር ገመድ ተቆራኝተዉ የቆሙ ይመስላል::” [ከአድማስ ባሻገር፥* 1967፥ ገፅ 55] የኤፍሬም ግድግዳ ከቁሳዊነቱ ይልቅ ማኅበራዊ እሴቱ ይደምቃል:: ርዕሰ ጉዳዩ በአንድ ሁለት አረፍተ ነገር ሊሚሸሽ ሲችል፥ ገጣሚዉ ረቀቅ ብሎ ሲቀኝበት እንቅልፍ የሚነሳን አስተዉሎት ይሆናል --ግድግዳዉ ድንበር፥ ሀገር አክሎ ይገዝፋል:: ሰዉ እንጂ፥ የተገደገደ የድንጋይ ክምር አርነትም ከርቸሌም ነዉ::

በህፃናት ምክር
ዛሬ ሳይ ተንዶ፥ ፈራርሶ የምናየዉ
ጣራና ግድግዳዉ
ነገሩ ነዉ'ንጂ
ጥንትም አቅም የለዉም በፍቅር የቆመ ነዉ
የዋህ በሚባሉ በስያቶቻቸዉ።[ገፅ 25]

Scanned by CamScanner

ባለቅኔ በ"የጆሮ ህመሜ መንገዉ ምክንያት" በተሰኘ ግጥሙ ይታዘባል፤ ጭብጥ በየጉራንጉር ሲፈላ፥ ሌሎች ግን ስንኝ ለማስገር መባዘናቸዉ ከነከነዉ። ለጥፋት ይሁን ለትንቢት፥ የዚህ ግጥም ቃላት አመፅ ሲያራግቡ ፈተኑት። በሌላ ግጥሙ "ዜር ሲደመር ዜር" ከምንም ቅኔ መንጠቅ ይቻላል ባይ ነዉ። ለግጥም ምትሀት ኖቤል የተሸለመችዉ ፖላንዳዊት -Szymborska " ቁጥር ፍለጋ ተራ ከሚጠብቁ ዜሮዎች ይልቅ፥ ብቻቸዉን የቀሩ ነፃ ዜሮዎችን እመርጣለሁ።" ብላ ነበር፤ ዜሮን እየፈለፈለች መደርደር። ኤፍሬም ዜሮን ጮቀን ለቀቅ ሲያደርግ ታግተዉ የነበሩ ቁጥሮች የሆነ ሸንቁር ጥሰዉ ሲያፈተልኩ ስንኝ ደቀነላቸዉ።

ምንም ከሚሆነዉ
ደርቆ ከምናየዉ፥ ከባዶ ላይ ቅዳ
ይህ ነዉ የህይወት ትርጉም፥ የመፍጠር ዕዳ
ምንጩም ባዶ ባይሆን፥ መቅጃዉ ነዉ ቀዳዳ።
[ገፅ 110]

መጀመሪያ ያነበብኩት ለስብስቡ ርዕስ የታጨዉን "ኑ... ግድግዳ እናፍርስ" ሆነና ወደ ሌላ ገፅ ለመሻገር አይፈቅድም። ሀዘንን እዉጭ ለመከተር ዙሪያችን የገነባነዉ ግድግዳ፥ ለመደሰት ምክንያት የሚሆነን ክስተት ጭምር ገድቦብናል የመሰለ አንድምታ ርዕሱ እየጠራ ያሳስተናል። እዉቅ ፍልስጤማዊ-እስራኤላዊ ገጣሚ ማህሙድ ደርዊሽ የመሰከረዉ ታሰበኝ። *"Poetry and beauty are always making peace. When you read something beautiful you find coexistence; it breaks walls down"* ላህይና ሥነግጥም ሰርክ ዕርቅ ላይ ናቸዉ። የሆነ ዉብ ፅሁፍ ስታነብ ተጣጥመህ ታዘግማለህ፤ ይህ ስሜትህ ስንቱን ግድግዳ ይንዳል የመሰለ ፍካሬ ከኤፍሬም ስንኞች አይዘልቀንም -- የማያፈርሱት፥ ዘብ የሚቆሙለት ግድግዳ አለና። የደም ግባትና የቅኔ መፈቃቀድ እንዳለ ሆኖ።

Scanned by CamScanner

*አባይ ወንዝ አይደለም*
*ምድረ-በዳ የሚከድን ረጅም ምራቅ ነው*
*የሀበሻን ተንኮል*
*እግዜር ተፀይፎ-መሬት ላይ የተፋው*::[ገፅ 30]

እግዜር ተፀይፎ-መሬት ላይ የተፋው -እንደ አዋሽ- አልተካዉም? ለምን ይህ ምስል ሌላ ወንዝ -እንደ አዋሽ- አልተካዉም? የእስከ ዛሬ 'አባይ' አፈር እየናደ ባዕድ የመቀለብ ቁጭት ለትፋት፥ ለሀበሻዊ ተንኮል ዳርጐታል:: እንዲህ የተንዠረገገ ተንኮል አለ ወይ? በ"በግራጫ ቀለሞች" ረዘም ባለ ግጥሙ፥ የሚያወያዩ ምስሎች ተፈቃቅደዉ፥ ለቅርፅም ለጥልቀትም ይነበባል::

ለፍፁም ዝምታ ህሊናዉን ሰጠ
ካራት የህይወት ቀለም ሀሳብ በጠበጠ
እነርሱም
ህይወት አስጠልታዉ
መርዝ የተጐነጨ ያራት ዓመት ህፃን፤
ሸበት ጉንዳን ሆኖ
እናቱን የበላዉ ግዙፍ አረጋዊን፤
ሁለቱ ደግሞ
ሰዉ መሆን የሴለዉ የሴትነት ዉበት፤
እና
ከኔ በላይ ዕዉቀት ካምላክ ጋር መሟገት
ብላ የምትጮህ የባቢሎን ንግሥት
ነበሩ::

... እያለ እስከ ዝምታ ይጨምታል:: *"sometimes the most powerful thing you can say is nothing at all"* ተብሏል:: አንዳንዴ የከበደ ሃሳብ ለማፍረጥ የምትበቃዉ፥ አፍህን ስትሎግም ብቻ ነዉ እንደ ማለት:: በበዛ *ጋጋታ* የተጨቆነን ዝምታ መተርጐም መቻል ባለቅኔን ይፈትናልና እስቲ ኑ፦ ግድግዳ እናፍርስ -- የሰብሰቡን ምስጢር ለመፈልቀቅ መደመም ከበጀን::

## ክቡሩን ሰለ ማክበር በሚንተባተብ ብዕር ፡ –

*ግጥም*

መነሻ ምክንያቱ ምንም መድረሻ በአቱ የትም ፤ ተጽፎ ቢታይም በጠይም ብሩና ማደሪያው ስስ ልቦና .....

*ግጥም*

ሃብትነቱ እረኞችና ነገስታት ፣ ወልዮችና ነብያት ። መገለጫ ምኩሩቡ ሕይወት ፣ መቅደስ እና ቤተ መንግስት እንዲሁም የሰው ልቡ ፤ መንፈስ እና ቀን ሃሳቡ ።

*ግጥም*

ነፍስ የምትጎነጨው የሃሳብ ወይን ፤ መሸተኞቹ ጥቂቶች የተመረጡ፡ወደ ጉባኤ የሚመጡ ። ስካሯቸው ፍፁም ሃሳብ ፤ መውደቂያ አልጋቸው ፍቅር እና ጥበብ ለሆኑ የተሰጠ...

*ግጥም*

ከሩሱ ጋር ለተማመኑ ፤ ነፍሱን በሸንገላ ላልሸመኑ የሆነ ። በሰገነት ሲነገር በጥቂቶች እዝነ ልቡና የሚንቆረቆር ። የሃሳብ ምንጭ ። የነፍስ ድርቀት ያጠቃው ሚጠመቀው...

*ግጥም*

መፃዒውን መግለጫ ፣ ስህተትን መቅጫ ። አርዓያነትን ማምጫ መንፈሳዊ በትር ፤ ከንጉሠ እስከ ህዝብ ማንንም የማይምር

*ግጥም*

ታዳሚዎቹ ብዙዎች ሳይሆኑ የተመረጡ ጥቂቶች ልብ የሚሉትና ወደ ልብ የሚልኩት ። በብቸኞች ቢፃፍም ወገን ዘመዱ እውነት

Scanned by CamScanner

ይህ *"በከፍተቱ መሃል"* *ከሚለዉ ግጥም* የተጠቀሰዉ ቅርፅና ይዘቱ *እንቀባበለዉ የነበርን የአማርኛ ግጥም* ይጋፋል:: ስንኞች *(ተቆፈረ / ተቀበረ)* ቤት ተራርቀዉ *ዜማ ቋጥሯል* እንጂ አልተሰካኩም:: ዉስጠ-ምት - ለመምታት ሲባል ተጠርበዉ *rhythm- ዜማ እንዳይነፈገ* ድማት የመግረፍ ያክል ሳይጣረስ ይደመጣል:: *[ራሱ ጥበቡ፥ ራሱ እዉቀቱ፥ ራሱ እዉነቱ እግዜር ተቀበረ ] -ራ ራ ... ሱ ቡ ቱ ...* ማንኪኪት የመሰለ ከፊል ዜማ ሳይነክስ እሳቦቱ፥ የእግዜር መቀበር፥ ሄዋን በሰይጣን አፈታሪክ ሳትከናነብ፥ የሰዉና የፈጣሪ ፊት ለፊት መላተም አልከሰመም፤ ምልክት፥ ፈለግ አስተርፏል:: እምነት ሆነ አለኝታ ሲፈረካከስ፥ ግጥሙ ለመፍረስ ስንኞች ሲያዳልጣቸዉ፥ አምላክ የእንስት ዉበት ሲያጠበረብረዉ ጉድጓድ ተቆፈረለት:: የአስተሳሰብም፥ የመቀኘትም ጭብጣዊና ቅርፃዊ ነፃነት አልተገደበም:: *በ የኢትዮጵያ ጥናት መጽሔት* (ቅጽ 36፥ ቁ. 2) አመሀ አስፋዉ *"አረፍተ ስንኝ"* የሚሉትን ከተዋስን የመጀመሪያ ሶስት መስመሮች እስከ *ተቆፈረ* አንድ አረፍተ ስንኝ ይወጠዋል ቢዘረጋ፤ ለጣቂ ሶስት ስንኞች እስከ *ተቀበረ* ሁለተኛ አረፍተ ስንኝ ነዉ:: *"አረፍተ ስንኝ፥ በአራት ነጥብ ወይም በእኩያዎቹ የሚደመደም የስንኞች ስብስብ ነዉ ..." [ገፅ 16]* አቅማማ እንጂ ኤፍሬም ለአማርኛ ሥነግጥም የረቀቀ prose poem ወይም *ዝርግ-ግጥም* ማፅደቅ ይችል ነበር:: ሀረግና ስንኝ በየግጥሙ ለሚነዝር ሆነ ለቀዘዘ ሁነት፥ ሥነልቦናዊ መቼት እንደ እንቅስቃሴዉ ምት፥ ይኮማተራሉ፥ ይለጠጣሉ እንጂ በማስመሪያ አይለኩም:: ይህ ኤፍሬም ሥዩምን ከአማርኛ ገጣሚያን -አንጋፋ ሆኖ ዘመነኛ-ነጥሎ የግል አምባ-ከፍታ አበጀለት:: ሰይፉ መታፈሪያ ስንኝን እንደ ግጥሙ ርዕሰ ጉዳይ ቢሸነሽነዉም ዜማ የተደለዘ በሆነ ንባባዊ ድርቀት፥ ግጥም እና ዝርዉ ይተካካሉ:: ሰሎሞን ደሬሳ በጥቂት ግጥሞቹ አመፀ እንጂ ከነፃ ግጥም ስልት



በበለጠ ለነባር አድልቷል፤ ይልቅ ያደፈረሰዉ *-እሽቅድምድም-* በሚል እጅጉን ዉብ ዝርዉ፥ ስለ *ሥነግጥም* ምንነት የተነተነዉ አዲስነት ነዉ:: የግጥሞቹ ርዕሰ ጉዳይ ለዘመኑ ሆነ ለዛሬ ያልተለመዱ ነበሩ፤ አንዳንዶቹ ከግላዊ ህይወት በተመዘዘ ስበዝ ይደፋፈናሉ:: በአማርኛ *ሥነግጥም* ኤፍሬም የቀነበበዉ አዉድ፥ ሰፊ ጥናት ይሻል፤ ይህ ሃሌታ ንባብ ስልሆነ እንደ ጡቀማ ይሰመርበት:: የኤፍሬምን የእይታ ሆነ የዘዬ አዲስነት ለማጤን በተለይ የሚነበቡ ግጥሞች አሉት:: "የሰባቶች አባት" ፥ "ስልስቱ ምስጢራት" ፥ "ግራጫ ቀሰሞች" ፥ "ብቸኝነት" ፥ "ኑ... ግድግዳ እናፍርስ" ፥ "ሙዚቃው" ፥ "የፍስጋ ህመም" ፥"ዉበት ከመታመም" ፥ በሌላ ግጥሞቹም የሱ ብቻ የሆነ አንጓ ወይም ስንኝ ቅኔን ይመጥናል::

የዚህ ስብስብ ግጥሞች ከአንድ አምስቱ በስተቀር ሲነበቡ አይሰለቹም፤ ዳግም ስንተዋወቃቸዉ ጥያቄ መቀስቀሳቸዉ፥ ጥበባዊ ዉበት ማፍለቃቸዉ አይግገታም:: የኤፍሬምን ብዕር የማይመጥኑ አንድ አምስት ግጥሞች ፈዘዉብኛል:: "የድሆች መፅናኛ" ፥ "ዝና" ፥ "ፍስጋ"፥ "የራሱ ዓለም ሰዉ" እና "ሁለተኝነት" ናቸዉ:: የስብስቡ ርዕሰ ጉዳይ ፍልስፍና፥ የማንነት ዕንቆቅልሽ፥ የሴት የፍቅር መዘዝና ፍካት፥ በሀገር ጉዳይ ለመመካትም ለማንጓጠጥም፥ማመንና መጠራጠር፥እንግልት፥በደልና መቦረቅ፥ አካባቢ ሰዉን መወሰኑ፥ ስዕል ግጥምና ሙዚቃ ለዉስጠት ማስታገሻነት...ተቀኝቶባቸዋል:: ዳኛቸዉ ወርቁ በ"*አደፍርሰ*" ልቦለድ የይፋትና ጥሙጋን አዉራጃ ሲገልጥ *"... ተራራ ላይ ሆኖ ሲመለከቱት እግዚአብሔር ዓለምን ሠርቶ ሲያበቃ የተረፈዉን ትርክምክም ያጕረበት ዕቃ ቤቱ ይመስላል::"* ብሏል:: ኤፍሬም በሶስት ገፅ ያክል አባይ እንደ እባብ በልቡ እየተሳበ በሌላ አገር መንገሱን የኮነነበት ግጥም፥ አንድ ሁለት ፍዝ ድግግሞሽ ደባበሰዉ እንጂ፥ ሃሳቡ ሣይሆን ምስሉና ድምፀቱ ድንቅ ነዉ፤ ሃሳቡ የተነገረ መሆኑ ላይታወሰን ይችላል:: ገጣሚዉ አበሻነትና አባይን ለማነፃፀር ሌላ እምቅ *ሩባኢያት* አስነብቦናል::

Scanned by CamScanner

ህፃናት ተጫዉተዉ
ለዋቂዎች በሰተዉ ጠገበዉ የሚያድረበት
ሰፈር
እዚያ ነበር።
[ገፅ 84]

ባለቅኔዉ ገለልተኛ ተመልካች ሳይሆን፣ "ስቅሶና ሙዚቃዉ የሚደለደ ሰፈርን ቅርፊቱ የተጋጠ መንደር፣ ከአዝቅቱ የሚወራጩዉን መፍለቅለቅ መጋረድ እንደማይቻል፣ ልቦናችንን በሚሰበስብ እንቅስቃሴ ይገዛናል። ዓለማየሁ ገላጋይ "በአጥቢያ" ልቦለድ የመሰመሳቸዉ፣ የሆነ የደስታ ሰንኮፍ ለመንቀል የሰቆቃ ክምር የሚያበጥሩትን (1999፣ ገፅ 116-133) የጋዩ ገፀባህሪያት መካከል፣ ኤፍሬም ዉብ ወጣት ሴት የአድራሻዋ መፋቅ ነዝሮት፣ መርፌዉን እንዳገኘ ክር የሆነ የተቦጫጨቀ ጎላዌ ለመጣፍ ተቀኘ።

እዐና መስተ ወንዶች በበሯ አልፈዋል
ባይተኗትም እንኳ
ለደናን ስይተዉ ብቻ አድሚ ቀጥለዋል።

......................................

መንደሯን የሞላዉ
የሚገርመዉ ግና
መሶብ ሙሉ ሰቃይ፣ እንስራ ሙሉ እምባ
የሆነዉ ደህ ቦታ፣
የመንገደኛዉን አይን፣ የመንገደኛዉን ልብ፣ ባዘን እያባባ
እሷ ግን ነበረች፣ ቀይ ስጊረዱ፣ የእሾህ መሀል አበባ
እናም ለዚያ ሰፈር
እናም ለዚያ መንደር
የርሷ መኖር ብቻ፣ ለሰፈሩ ሰዎች ሳቅ ይፈጥር ነበር
ተስፋ ይሰጥ ነበር
ጥጋብ ይሆን ነበር።
[ገፅ 84 ]



የተናደ መንደር፣ ሳይፈራርስም የጎላዌ እንግልት ያልገሰሰዉ ዉበቱ፣ በትግዛታ ተተክቶ አልተሻረም። ያማረ ሸጣጣ ህንፃ ቢበቅልበትም፣ ሎሬት ፀጋዬ "ይኸ እንደኔና እንዳንቺዉ፣ *የዉበት ዓይኑ የሰለለ / ሰማይ ጨለማ አንጂ፣ እሳት እኮ አደለም አለ / ያልታደለ!"* እንደተነበየዉ፣ ከደሳሳ ጉጆ ያጉነቆለዉ ዉበት መች ከሲሚንቶ ይፈልቃል? አጉጆ ተጠልሎ የነበረ ትዉልድ ገጣሚዉን መዝምዞታል። ወይስ ሎሬት አዲስ የተቆረቆረ መንደር፣ እንዴት ዉበቱ ደበዘዘባችሁ ማለቱ ይሆን?

ኤፍሬም በግጥሞቹ መካከል ነባር የቤት ቀለም ቆጠራ የመጠጡ ስንኞች ቢያገለግሉትም፣ በአመዛኙ ለነፃ ግጥም *-free verse-* ያደላል። ነፃ ግጥም ቤት ሲመታ፣ ሳይመታም ይችላል። የሀረግና ስንኝ ምጣኔ / እርዝማኔ ቀለም በመቁጠር ሳይሆን የክስተት፥የተናጋሪዉ አልያም የአፍታዎች ዉጥረትና መርገብ ኮሽታ የለጠጣቸዉ ያክል ይተነፍሳሉ። እላይ ከየግጥሙ የተቀነጨቡትን፣ ቅርፃቸዉን እንደ ስዕል ማስተዋል ይበጃል።

ከገነት ደጃፍ ሳይ
በሄዋን ዉብ ጣቶች
የጥበብ፣ የእዉነት ጉድጓድ ተቆፈረ
ሄዋን በሰራችዉ
በዛ ጥልቅ ጉድጓድ
ራስ ጥበቡ፣ ራስ እዉቀቱ፣ ራስ እዉነቱ እግዜር
ተቀበረ።
በዚህ ዉድቅት፣ ሂደት
በእግዜርና በሰዉ
በሁለቱ መሃል ግን እንደ ክፍተት ነበር
ምልክት የነበር።
[ገፅ 42]

ዉሻ ዉበቷን ሲያነፈንፍ፣ እሷ ተቆነጃጅታ የምትጠብቀዉ አንዷዬን ሳይሆን ያፈቀረችዉ ወንድ -*soulmate*- በመሆኑ አደባባይና ገመናዋ ይላተማሉ፡፡ አጭር ጊዜ መጠበቅ - ልቧ ለተጣደፈባት ሄዋን - ሙሉ ቀን፣ ሳምንት ካከለስ? መቅረት፣ አለመምጣት እንደ ህይወት ግራ የሚያጋባ የጊዜ መሰነጣጠቅ ሊመታዉ ይችላል፤ አፍቅራ ችላ ከተባለች ግን፣ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ማንነቷ ተበሳስቶ ትታወክ ይሆን?

ዘመም ካለ ጐጆ የሚርመሰመስ፣ ከመንደራችን የተላመድነዉ የፍቅርና የሽሽት ክስተት እንኳ፣ ኤፍሬም በስንኞች ትኩስነት ይለግሰዋል፡፡ የሆነ የጎላዊ ቁርጭራጭ ከብርሌ እምብርት በማጠራቀም፣ ለአፍታዎች ነቅንቆ ቢዘቀዝቀዉ ተፈናጥረዉ የሚበተኑ ቃላት የሉም፤መዘዝና እፎይታ ተደፍተዋል፡፡ በ"የፈረሱ መልኮች" ጠርዝ ላይ የተገፈተሩ -*marginalized*- ግለሰቦች ጓዳቸዉንና መንደራቸዉን ሳይታክት ያጤናል፤ በፊልም ካሜራ ተመርጠዉ ለስንኝ የተረፉ መልኮች አሉ፡፡

ፈርሶ ለማየዉ ቤት አራት ኪሎ ላለዉ፣
ሁኔታዉ
ክፍት የእንጨት አጥር
ትንሽ ገደድ ያለ፣ ልሙጥ ቆርቆሮ በር
መሳ ቅጥ የሌለዉ
ለቅሶና ሙዚቃዉ የማይለይ ሰፈር
ነበር፡፡
ግን
ፈገግታ የሞላዉ
በቤቱ ጥበተ ልክ፣ ደስታ የማያጣዉ
ግድግዳዉን የሚያልፍ ሃዘን የወረረዉ
ሳመት ባል
ሳመት ባል ዋዜማ ብቻኛ ቀናቸዉ
እፎይ የሚሉበት

## ቅድመ ፍልስፍና

ፈላስፋ ተነስቶ እግዜር የለም ካለ
አምላክ የለም ካለ
ፈላስፋው ልክ ነው
እግዜር ነው ፈላስፋው
ምክንያቱም...
እግዜር .. አንዱን አስነስቶ
አፉን በቃል ከፍቶ
እግዜር አለ ብሎ.. ሊያናግር ሲሻ ነው
ያን - የለም አስብሎ.. ቀድሞ ሚያናግረው



## ኑ ፡- ግድግዳ እናፍርስ

ከአፓርታማ ቤቶች
ሠማይ ጠቀስ ኑሮ
በጭቃ ተበክቶ
መሬት ላይ እሳካሉት የሣር ቤት ጓሮ
የሁለት አባ ወራ
የሁለት እማ ወራ
አንድ ግድግዳ አለ.. ደግሞም አንድ ጣራ
ሸበታም ያቀፈ ህፃናት ያዘለ ታሪክ የሚያወራ፡፡
እናቶች እህቶች ዝናብ ያስጠለለ
ጎልማሶች ወንድሞች... ፀሃይ የከለለ፡፡...
የሁለት አባወራ አንድ ግድግዳ አለ፡፡...
.....
በወዲያኛው በኩል
ጠርዙ ተሰንጥቆ ግድግዳው ተጎድቷል
ጣራውም ጭስ ጠግቧል
በወዲያኛው በኩል...
ጣራው ምንም አይልም...
ደግሞም ግድግዳቸው ለክፉ ባይሰጥም
ለዚያኛው ደህንነት
ለጎረቤት ህይወት መቀጠል ሲባል ግን መለጠፍ አይችልም፡፡
ምክንያቱም
ግድግዳው አንድ ነው
ጣራውም አንድ ነው
ደግሞም...
ለአንደኛው ቤት ውበት
ይህ ጣምራ ግድግዳ ይፍረስ እንኳን ቢባል
ያንዱን ቤት ገመና ፀሃይ ይሞቀዋል
ስለዚህ...
ግድግዳው አይፈርስም

Scanned by CamScanner

## ልዩነት

አንዳንዶች አይጠፉም
ስለ.. እውነት
ስለ.. እምነት.. ታስረው የሚኖሩ
በታጠረ ግቢ
ተወስነው ያሉ ፃይ እየተጋሩ፡፡
ቆመው የትም ያሉ
ነፃነትን ያሉ፡፡

*

ደግሞም መሃላችን ብዙች ይገኛሉ
ባሉበት የሌሉ
በሌሉበት ያሉ፡፡
ዘወትር አንድ አይነት÷ህይወት የሚኖሩ
በመብል በመጠጥ ሰብተው የወፈሩ
የሚንቀሳቀሱ
የትም የማይደርሱ...
የትም የሚሄዱ
ጥቂት እንደሄዱ.. የሚንገዳገዱ፡፡
(መሃል)
በሁለቱ መካከል
አለ ትልቅ ሚዛን ከፋፍሎ የሚጥል፡፡
በሚዛኑ ላይ ግን?..
አንዱ በአንዱ ወቶ ሲመዘን እንዳይችል
ይገኛል ልዩነት ሰማይን የሚያህል
የወርቅ
እና
የ'ህል፡

## የተፈታ ትዳር

*

የኛ ነው ከምለው ...የኔ ነው ብለሽኝ
አልማዝ እና ወርቁን
ብርና ነሃሱን.. ሁሉንም ወስደሻል...
ተመልሠሽ ነይ..
የኔ የማልለው..
አንቺ ያፈራሽው..
ዕንባዬ ቀርቶሻል፡፡

Scanned by CamScanner

ግጥም
ፈገግታን ፣ በፈገግታ መሃልም ከዕንባ ምንጩ
ከዕንባ መሃል የሚታይ የተሰወረ የማይገለጥ የተከደነ
የሚጠልቅ ። ረቂቅ ። ከእርሱ
የለም ተብሎ በመሠሀ የተመሰከረለት ሀያው...

ግጥም
ከአምስቱ ስሜት ህዋሶች በላይ የሆነው ሰባተኛው ስሜታችን ለአምስቱ
የሚልከው ፣ ልብ የሚል የሚቀበለው የነፍስ መልዕክት

ስለዚህም
ወደ ነፍሱ የተጠጋ ግጥምን ያፈቅራል በመልዕክት ያምናልና ከነፍሱም
የተጋባ ግጥምን ይጽፋል መልክዕክተኛ ነውና ።

እነሆ መልእክት ...



# እኔ

የነባር ፈላስፎች
ታላቅ ጥያቄ...?
'የዚህ ዓለም መኖር ምክንያቱ ምንድን ነው?'...
የሚል ነው፡፡
*
መልስ
የዚህ ዓለም 'መኖር' ተፈጥሮም መገኘት
ትልቁ ምክንያት
የ 'እኔ' መኖር ነው ይህ ነው ፍፁም እውነት፡፡
*
ስለዚህ...
የእኔ ህልው ሆኖ በዚህ ዓለም መኖር
ላ'ለሙ መፈጠር÷ ምላሹ ከነበር
እንደሌለሁ ማመን፡ የለሁም ማለትም
ሌላኛው መልስ ነው ውሉን አይስተውም
ምክንያቱም...
የለሁም ስላልኩኝ÷ይሄ ዓለም አይኖርም፡፡
*
ግን
ድንገት
ሆኖ የተገኘ...
አልሆንኩም ማለቱ መሳሳት ከሆነ
ታላቁም ጥያቄ
የፈላስፎች ሳይሆን - የሕፃናት ሆነ፡፡

Scanned by CamScanner

ያ.. አንዱ ጣሪያ… ያ…አንዱ ግድግዳ
በዚያ ጎጆ በኩል…
ለሚመጡት ሁሉ …
አስቀምጦ አለፈ.. መከፈል የማይቻል እጅግ ታላቅ ዕዳ፡፡
ሰላም የጠፋበት
እንቅልፍ የጠፋበት
ሃፍረት የሞላበት…
ድህነት እንደ መብት.. የሚዘመርበት
ገመና… እንደ ፀሃይ ለዓለም የሞቀበት…
በዚያ ቤት የሚያልፉ አንገት ሚደፉበት…
ሆነውና አረፉት፡፡
የሚገርመው ነገር
ከዚህ ፍርስራሽ ቤት.. ከወለሉ መሃል…
አያቶች የፃፉት
ልጆች ልብ ያላሉት.. አንድ ቃል ይገኛል….
“በዚህ በኛ ጎጆ ለምትመጡ ሁሉ
ይህን ልብ በሉ…
የዚህ ቤት ግድግዳ…
ምሰሶ ማገሩ… ታሪክ መሰረቱ
የአብሮ መኖር ምስጢር.. ውልና እውነቱ
አያልቅም ተነግሮ..
አያልቅም ተዘክሮ.. በዚህ ዘመን በኛ…
ደግሞም ለግድግዳው…
ለምሰሶው ስንል.. ‘የሞትንም እኛው ነን.. የገደልንም እኛ’ …
ነገር ግን ምንአልባት…
እኛን ሞኝ አድርገው
ቃላችንን ንቀው…
ትውልዶች ቢነሱ…
ግድግዳ ሲንዱ.. ግድግዳ ሲያፈርሱ
እናንተ….

Scanned by CamScanner

ፈራሾች ዝም አሉ
አፍራሾች አዘኑ እጅግ ተሳቀቁ
በመከሩት ምክር…
ከነዚያ ጋር አብረው በአንድ ሥሎ'ደቁ፡፡
በዚህ ታላቅ ስህተት
በዚህ ታላቅ ጥፋት
ማንም አልተጎዳም
ደግሞም የትኛውም ሊጠቀም አልቻለም፡፡
ይልቅ…
ግድግዳው እንዲፈርስ
የመከሩት ቤቶች… ዶማ ያነሱለት
ጨረስን ያሉለት…
ዶማ የጣሉለት…
ከዚያኛው ቤት ይልቅ…
የነሱን ነበረ…
ፀሃይ ያጋለጠው የነውራቸውን ሃቅ፡፡
በህፃናት ምክር…
ዛሬ ላይ ተንዶ… ፈራርሶ ምናየው
ጣራና ግድግዳው…
ነገሩ ነው'ንጂ…
ጥንትም አቅም የለው በፍቅር የቆመ ነው
የዋህ በሚባሉ በአያቶቻቸው፡፡
…
ይኸው ከዚያ ኋላ…
ለብዙ ዘመናት…
በሰላም የኖረው
የሁለት አባወሮች
የሁለት እማወሮች … ህፃናት ያዘለ
ፀሃይ የከለለ
ዝናብ ያስጠለለ



Scanned by CamScanner

ይፍረስ ቢባል እንኳን
የዚኛው ቤት ሀዘን...ለዛኛው መትረፉ በፍፁም አይቀርም::...

...
እኚህ ሁለት ቤቶች
ሁለት አባወሮች
ሁለት እማወሮች...
ይተዋወቃሉ..
ምንም ሳያወሩ.. ቃል ሳይሰነዝሩ
አንደበት ነውና.. ምሰሶ ማገሩ::
እና?
ከዘመናት ኋላ.....
የአባወሮች ወንዶች
የእማወሮች ሴቶች
ከአንዱ ቤት ጣራ ስር እንደዚህ መከሩ
ድምፅ እያወፈሩ
እዚያ ቤት ያሉትን በዛቻ ሊያስፈሩ
አብረው እንዳልኖሩ
...
"ኑ ግድግዳ እናፍርስ
ኑ ግድግዳ እንደርምስ
የዚያን ቤት ገመና..
የዚያን ቤት ምስጢር..
ተሰውሮ እንዳይቀር.. ከአደባባይ ይደር!"
እናም
ግድግዳ ሊንዱ..
ግድግዳ ሊያፈርሱ
ከሩቅ ጎረቤቶች
አካፋና ዶማ ሄዱና ተዋሱ
በውሰት መሳሪያ...
በዶማው አፍርሰው በአካፋው ሲዝቁ

# አባይ ፩

አባይ ወንዝ አይደለም
ምድረ-በዳ የሚከድን ረጅም ምራቅ ነው
የሀበሻን ተንኮል
እግዜር ተፀይፎ-መሬት ላይ የተፋው።።

# ሠባት ወይ

ከሠባት ከፍ አ
ከአምስት ዝቅ
መፈጠር ብቻ
ሕይወት የሚ
(በዚህ በኛ ሀገ
አልገባኝም አለ
በጠየቀ ቁጥር
ሰባትን የማያ
አምስትን የማ
ወይስ... የዚህ
ምንም... ምን
ምኑም አልገባ
ምንድ ነው ከ
“የሕዝቡ ልብ
የ’ሕይወት ም
ወይስ አልቦ ቅ
ምኑ..?..
አለ ሌላው
እንደ-ሊቅ-አው
ገና ሳትናገር ገ
ትንሽ ስትናገር
እርሱን አይደል
ምኑ?..
አለ..ሌላው።።...
ምኑ ማለት መ
ምንም ምኑም
ከሠባት ከፍ አ
ከአምስት ዝቅ

Scanned by CamScanner

እኛን የምትወዱ
ለእኛ የምትሳሱ
ያኔ… ደም አልቅሱ!!!…
ምክንያቱም…
ይኸኛው ተነስቶ ጠላት ሲሆን ለርሱ
ጠላት ሆኗል እና… ለገዛ ለራሱ ።
እናም.. ደም አልቅሱ!”

Scanned by CamScanner

# መሰንቆና—ብቸኝነት

ከሠዓታት-በፊት…
ካ'ዝማሪ ቤቱ- ሥር
የአንድ የወጣት ነፍሥ… ለብቻዋ ቆማ
ፍቅርና ትዝታን…
ከዕድሜዋ በላይ.. ባሳብ ተሸክማ
መጠን አልባ ርቀት
ሰው አልባ ዓለማት
(ተጉዛ-ነበረ)…
ድንገት ከመሃል ግን…
መሠንቆና ዜማ ይጠራት ጀመረ፡፡
…
ይሔ ክቡር ወጣት.. የሀሳብ ጓደኛ
መሠንቆ መቺውን…
ወዲህ ቅረብ አለው.. ወዳ ጥግ ወደኛ፡፡
…
ማነህ የክር አባት..የሙዚቃ ጌታ
ዜማህን ከፍ አርገው…
ግጥሜን ተቀበለኝ መሰንቆህን ምታ
ያዝ…
ያዝ በል ተቀበለኝ…
'አንድ የመሰንቆ ክር የመሰንቆ ገመድ እየገዘገዘ
ተስፋን የተሞላ ብዙ ድምፅ አውጥቶ ልቤን አፈዘዘ፡፡…
እናም…
ካንድ ሰው ዕልፍ ሀሳብ… እንዳልተወጠነ
ውጥኑ ሀሳቤ በክርህ ሙት ሆነ
እድሜ ለሙዚቃ..
እድሜ ለሙዚቃ…
ካንድ ክር ዕልፍ ድምፅ እየተወጠነ
ብቸኝነት ጠፍቷል ደመና እየሆነ፡፡



Scanned by CamScanner

ብዙ ነገር ቁጠር
የሴት ጥበብ ቀመር
ግራ ሊጋባህ ነው....
የሚመጣው መሪ የኮከብ ቁጥር ነው
ከእምነት ከፍ አይልም
ከሠባት ዝቅ አይልም...
"የምን መሪ?" አለ... ቅድም የጠየቀው
"እርሱን አይደል ምልህ" እያለ የሚያወራው
"መልሱን ሣትናገር.. ገብቶኛል" የሚለው
እንደ ሊቅ ጠይቆ... ደንቁሮ ሚሠማው...
የምን መሪ አለ...
ታድያ.......
እኔ
እርሁን በማስረዳት ዕድሜ ልጨርስ ነው...?
እስኪ ጊዜ ይፍታው!

Scanned by CamScanner

# ሠባት ወይም አምስት

ከሠባት ከፍ አይልም...
ከአምስት ዝቅ አይልም
መፈጠር ብቻውን ሕይወት አይባልም
ሕይወት የሚባልም ምንም ነገር የለም።...
(በዚህ በኛ ሀገር)
አልገባኝም አለ...
በጠየቀ ቁጥር ሊቅነት ሚመስለው
ሰባትን የማያልፍ
አምስትን የማይተርፍ የሕዝቡ ቁጥር ነው
ወይስ... የዚህ ግጥም ቤት መምቻ ሐሳብ ነው...
ምንም... ምንም... ምንም
ምኑም አልገባኝም
ምንድ ነው ከፍ አይልም..
"የሕዝቡ ልብ ነው
የ'ሕይወት ምርምር . ነው...
ወይስ አልቦ ቅኔ የመፃፍ ስልት አለው?"
ምኑ..?..
አለ ሌላው
አንደ-ሊቅ-አውርቶ-ደንቁሮ ሚሠማው
ገና ሳትናገር ገብቶኛል የሚለው
ትንሽ ስትናገር...
እርሱን አይደል 'ምልሁ-እያለ 'ሚያወራው
ምኑ?..
አለ..ሌላው።...
ምኑ ማለት መልካም
ምንም ምኑም ምንም
ከሠባት ከፍ አይልም
ከአምስት ዝቅ አይልም... እንዳሰኘህ መርምር



Scanned by CamScanner

(እናም.......
በፀጉሯ ሰቀላት
በፀጉርዋ ሲሠቅላት.....
ምርጥ ሐሣብ መጣለት....
(ጥቂት አረፍ አለ...
ሐሣብ በጠበጠ
ዳግም ተመሰጠ
ሕይወት ቀላወጠ...
ሳላለቀው ሥዕል አራት ዓይኑን ሰጠ

.....
ይህችን ውብ እንስት...
የዘፈን ምሁራን ውበቷን ሲገልፁት
የሣር መሃል መንገድ ያ'ንገትሽ ርዝመት
ዘንባባ ቁመትሽ
ከዋክብት ዓይኖችሽ....
የሚላት ዓይነት
ናት፡፡
ልጅት
በፀጉሯ ተሰቅላ ዋርካ ላይ ምናያት፡፡
ሠዓሊው...
ሰቅሏት እንዳይገድላት
ሣሣላት፡፡
እናም...
በፀጉሯ ሰቀላት...
በፀጉሯ ሲሰቅላት...
ጭንቀቷ ቢበዛ ጣሯ ቢያሰቃየው
ልጅቷን ቢወዳት
ልጅቷን ቢያፈቅራት
ልጅቷን ቢያዝንላት
አንገቷ ላይ ታንቆ ራሡን ሰዋላት
ራሱን ቢሰዋ ...ራሷን ገደላት
ከከንፍር የማይዘል የሠዓሊ ብልሃት
የሚገርመው ነገር...
ይህንን ሲሠራ...
የሚሥለው ግጥም



ለሚፈጥረው ዓለም... ያሰፈረው ቀለም...
፩
ፀሐይ ሣይዳስሳት
ዝናብ ሣያርሳት
አልኮል ሣይጠጡባት
ውብ ሴት ሣያቅፉባት...
ያላንዳች ጨዋታ ያለሳቅ ያለፈች የቅዳሜ ዕለት
እና
ሁለተኛው...
ብዙ ድብልትልቆች...
የከፉ ሠው ፊትን ልብ ያሉ ሕፃኖች
፪
ሕይወት ሥትሰክር ሞት በርጋታ ሲጓዝ
ባህር ዋና ሲሔድ ብርሃን ሲቀዘቅዝ
እንዲሁም...
አራተኛው ቀለም....
በጠራራ ፀሐይ
ምንገድ ዳር የተኛ የጎዳና ፋኖ
እና....
ከመነሻ በቀር...
መድረሻ የሌለው የአመሻሽ ጉዞ
(ነበሩ)፡፡....
እንግዲህ....
ከዚህ ሁሉ ኋላ....
ከኔ በላይ ዕውቀት ካ'ምላክ ጋር መሟገት
ብላ የምትጮህ የባቢሎን ንግሥት
ከጫጫታ መሃል በሚገኝ ጫጫታ
ብሩሿን አንስታ ቀለሜን አጠፋች
በእርጅና ዘመን
ዳግም በሚፈጠር
በልጆች ጨዋታ ትርጉሜን አዛባች
እናም ለኔ ግጥም
እናም ለኔ ሥዕል
እንዲህ የሚነበብ ርዕስ ሰጠችኝ
አበቦች አስጠሉኝ
ለምለም አረንጓዴ ቅጠሎች ቀፈፉኝ፡፡

ስለ ሸራ ፈንታ ወረቀት ዘረጋ
በቀለሞች ምትክ ብዕሩን አነሳ…
ትዝታውን ሊፅፍ…
(በተቀመጠበት…
ለፍፁም ዝምታ ሕሊናውን ሰጠ
ካ'ራት የሕይወት ቀለም …ሐሳብ በጠበጠ
(እነርሱም…..)….

ሕይወት አሥጠልታው
መርዝ የተጎነጨ ያ'ራት ዓመት ሕፃን…
ሸበት ጉንዳን ሆኖ…
አናቱን የበላው ..ግዙፍ አረጋዊን..
ሁለቱ ደግሞ…
ሰው መሆን የሌለው የሴትነት ውበት
እና…
ከኔ በላይ ዕውቀት ካምላክ ጋር መሟገት
ብላ የምትጮህ የባቢሎን ንግሥት
ነበሩ።….
•••
(እናም)…..
እኒህ ተበጥብጠው
እኒህ ተደባልቀው
እንባን ባይኑ ሞልተው…
ወረቀት ሸራው ላይ… በዚህ መልኩ ሣለው።…
ንድፍ…
አንድ ትልቅ ዋርካ ዕድሜ ጠገብ እንጨት
ወፍ የማያርፍበት ጉጉት የበዛበት
ከዋርካው ላይ ደግሞ የውብ ሴት ሥቅለት
ሴቷ አንገት ላይ ደግሞ…
የሌላ ሰው ሥቅለት ….የሌላ ሠው ሕልፈት
ይታያል…
ብራናው ላይ ፊደል
ፊደሉ ላይ ምሥል



ከምሥሉ ላይ እውነት….
የሕይወት የሕልፈት የውበት አዝመራ
በፊደል የሚታይ በወረቀት ሸራ
ይገኛል።….
ልጁ….
ለፈጠረው ዓለም
የሚሥለው ግጥም
ከሕይወት የቀዳው የደፈረው ቀለም
፩
ጋዜጣ ሣይገዙ
መጽሐፍ ሳይገልጡ
ያለምንም ተግባር ያሣለፏት ዕለት
እና
፪
ባለው ብር ጠጥቶ
ቦርሣውን አራቁቶ
(ካደረ በኋላ)…
፫
ራስ ምታት ይዞት…
ለቡና አቅም አንሶት…ቆሞ ሚንከራተት
ዕሁድ ከሠዓትን…
የሚመሥል ዓይነት የምስኪን ሰው ሕይወት
ነበር።
የግጥሙ ስዕል…
እንደ ጭንቀት ሌሊት የፀጉርሽ ርዝመት
የሚሉላት ዓይነት…
የልጅቱን ፀጉር…
አንድ ላይ ጠቅልሎ እጆቿን ጠፍሮ
ከ'ጇ
የተረፈው ዋርካ ላይ ተቋጥሮ
ይታያል።….
ሠዓሊው….
ልጅቷን….
ሰቅሏት እንዳይገድላት
አዘነ ሳሳላት

Scanned by CamScanner

## ሠለስቱ ምስጢራት

እናም…
እኒህን ሦስት ምሥጢሮች ስነግርሽ
አልገባኝም እንዳትይ ነው…
አደራ የምልሽ
፩…
አንደኛ ልንገርሽ
ምንም ያልነገርኩሽ አንዳች ምስጢር የለም
ሁሉን ሰምተሽዋል..
አብረን ከዚህ ቀደም፡፡
፪…
ሁለተኛም ያው ነው
ራሱ ምስጢሩ… ከየት የመጣ ነው?
፫…
ሦስተኛው ነገር ግን የልቤ ላይ ፍሬ
የገመትሽው ካለ… እርሱ ነው ምስጢሬ፡፡



## አብዮት

ከዚህ ሁሉ ኋላ…
ወይናችንን ንቀን ጫጫታ ቢወገድ
ተመስጦን አርምሞን ሕሊናችን ቢለምድ…
ዝም ማለት ብንችል ለጥቂት ቅፅበታት
ከሕሳቡ በላይ እርሱ ነበር ዕብደት፡፡

ያላየሽኝ ዕለት...
ሳምንት እና ዕለቱ ካለፉ በኋላ-ተገናኘን እና
አንቺ ማክያቶ÷እኔ ጥቁር ቡና
እየጠጣን ሳለ ...
ሶስተኛዋ ልጄን አርግዠለሁ አልሽኝ
ስም አወጣንላት 'ናፍቆት' እንድትሰኝ

፬

ከኔ ጋር ተኝተሽ
የሌላ ስም ጠራሽ የእኔን የሚመስል
ካንቺ ጋር ተኝቼ
የሌላ ስም ጠራሁ የአንቺን የማይመስል
አራተኛ ወለድሽ
'ማየት መልካም' ብለሽ...
ማየትን ስንወልድ...
አዲስ ነገር የለም ሁሉ እንደነበር ነው
አምና እንደ ዘንድሮው
ዘንድሮም እናዳምናው
ሰው ነው የሚጠፋው አይንና ህሊናው።
የአምሮት የምኞት በኖበት ዐቧራው

፭

አምስተኛ ልጄ
ልክ እንደ ንቅሳት...
ሁሌም የማትጠፋ ከልቤም ከእጄ
ከሁሉም አብልጣ ብቸኛ ወዳጄ
አምስተኛ ልጄ...
አንቺን መሳይ ሆና
ውበት.. ደም ግባትዋ..ተክለ-ቁመናዋ
'ቅናት' የምንላት የስም መጠሪያዋ!!..
የሚገርመው ነገር
ቅናትን ስንወልድ ቤታችን ደረጀ





ቅናትን ስንወልድም ፍቅራችን አረጀ።

*

፮

አምስቱን ወልጄ እኔስ መች እርም አልኩኝ
ማየት መልካም ብዬ ሌላ 'ስም' ደገምኩኝ
የሚገርምሽ ነገር
ለእኔ እና ላንቺ በር
ይሄ ምስጢር ነበር።
የደገምኩኝ እለት÷ማታ ስንገኛኝ
አንቺ አታውቂም እንጂ...
ለሙቀት ለእቅፍሽ አዲስ ሰው ነበርኩኝ
አንቺ አታውቂም እንጂ
ይህ ነበር ጥበቡ
ይህ ነበር ምክንያቱ
የተሰኘሁበት የ'ፀፀት' አባቱ።

*

፯

የሚገርምሽ ነገር
ሳላቅ መስሎሽ ነበር ሥገባ ባንቺ በር
እኖራለሁ እንጂ የማያውቅ መስዬ
እኖራለሁ እንጂ
ምስጥሬን በጉያ በእቅፌ አዝዬ
የፍቅር.. የእልህ.. የናፍቆት.. የማየት..የቅናት.. የፀፀት..አባት ነው ተብዬ
እኖራለሁ እንጂ
አሜን ብዬ
ይሁን ብዬ.. ተቀብዬ..
እንጂ
እንዳትሳሳቺ
እኔ- አሳዳጊ እንጂ..
የሠባቱም አባት 'ሰው-መሆን' ነው ስሙ.. ማወቄን ተረጂ።

# በክፍተቱ መሃል

ከገነት ደጃፍ ላይ
በሄዋን ውብ ጣቶች
የጥበብ..የእውነት ጉድጓድ ተቆፈረ
ሄዋን በሰራችው
በዛ ጥልቅ ጉድጓድ
ራሱ ጥበቡ..ራሱ እውቀቱ.. ራሱ እውነቱ እግዜር ተቀበረ፡፡
በዚህ ውድቀት.. ሂደት
በእግዜር እና በሰው..
በሁለቱ መሃል ግን.. አንድ ክፍተት ነበር
ምልክት የነበር፡፡
ያልታደለ ፍጥርት
እውቀትን
እውነትን....ጥበብን ሊሠፈር
ዕልፍ አእላፍ መልአክ በሠው ቤት ሊዘምር
ያለ ሥፍራው ገብቶ ተሠልፎ ነበር፡፡

Scanned by CamScanner

## ፍቅር ምን መሰለሽ?

እንደፅጌረዳ እንደ ሱፍ አበባ
በመልካም ጠረኑ መንፈስ እያዛባ
አጥብቀው ሲይዙት ሊሰበር ያዘማል
ትተው እንዳይሄዱ በመዓዛው ያስራል
ፍቅር ምን መሰለሽ?..
ዕድሜን ማባበያ ዘመን መሸንገያ
ህልምን ማሳጠሪያ የአምላክ ስጦታ
ብዙ መሻቶችን አስሮ የሚገታ፡፡
ይህን አላውቀውም..
ከማውቀው ነገር ላይ የምነግርሽ ነገር
አበባ ታቅፌ ዘላለም እንድኖር
ወይም ጣቴ መሃል አበባ እንዲሰበር፡፡
ትዝታስ ምንድ ነው?
ትዝታ ቅገርት ነው..
የሆኑትን ነገር ባልሆንኩት የሚሉት
ወይም አሁን ቢሆን ብለው የሚመኙት
ግን
ይህን አልፈልግም..
የዘመን አስታዋሽ የአበባ እርጋፊ ደራርቆና ወድቆ
ተመልከት እንዳይለኝ ..ውበትሽ ላይ ስቆ
አንቺ ላይ ተሳልቆ፡፡
ይህ ሁሉ ቢሆንም..
ውበትዋ ለከዳት ጠውላጋ አበባ ውሃ እሆናለሁ
የሕይወትን ንፋስ እተነፍሳለሁ..
እርጅናን ለመግደል ውቢቱን አበባ መፃፍ እችላለሁ
ፍቅር ምን መሰለሽ? ...

## ተስፋ

ሰማይ ከሰል መስሎ
ዕንባን ልቡ አዝሎ
መብረቅ አሰምቶ
በሰባ 'መት÷ ንጉሥ ፍጥረት ላይ ደንፍቶ
ሳይዘንብ ከዋለ
ሳይዘንብ ካደረ
የገበሬ ልቡ
በዝናቡ መቅረት÷ፍርሃትን ከጫረ
...መሬት ጦም ከዋለ
ተስፋ ከሰለለ
ተጠያቂው ማ'ነው?
እግዜር ነው?
ሰማይ ነው?
ጥፋተኛ ተብሎ ከሸንጎ የሚቆመው፡፡
* * *
የሰማይን ጥቁረት ተስፋ ላደረገ
አንገቱን አስግጎ ዝናብ ለፈለገ
ለምስኪን ጦም አደር
...ለራብ ለችግሩ ተጠያቂው ማነው
እግዜር ነው?÷ተፈጥሮ
...ተስፋ ጦም ካደረ መሬት ተቆፍሮ፡፡

Scanned by CamScanner

ቀኝ እጆዋን አንስታ ፀጉሯን ዳበሰች
ወደ ግራ እግሯ ቀኝ እግሯን ደረበች
የእርሷ
ቀሚሷ ከፍ አለ ጭኗ በጣም ጎላ
የርሱ
ወንድነቱ ሞቀ ጉንጩ ከፍም ቀላ
እርሷ
ከቦርሳዋ መሃል ቻፒስቲክ አውጥታ ከናፍሯን ቀባች
ከንፈሯን በከንፈሯ እየደባበሰች
ያም ሆነ ይህ ግና ? ያሳዝናል አለች
በጣም ያሳዝናል
ጨጓራን ይልጣል
ጉበትን ያበግናል
ቆሽትን ያሣርራል
ደግማ ጠየቀችው
ኧረ ለመሆኑ መቼ ነው ? አለችው
...
እርሱ
አንገቱን ሰበረ
ማውራት ተቸገረ
መቼ ነው ብለሽ ነው
የሰው ልጆች ጥንትም በፊት ስንጀምር
አምላክ በመዳፉ ሲሰራን ካርብ አፈር
ጊዜን ስንጀምር ጊዜ ሸሽቶን ነበር
አየሽ የኔ እመቤት
ባናውቀው ነው እንጂ ወይም ብንንቀው
ጊዜ ሚገነባው
ጊዜ እየሞተ ነው፡፡
ብራ ፀሐይ ያልነው ፈጥኖ እየዳመነ
ተጀመረ ያልነው ፍፃሜ እየሆነ

በጊዜ ጀርባ ላይ
ጊዜ የዕለት ስሙን ለወጠ ብንልም
ሁልግዜም አሁን ነው ሌላ መቼ የለም!!
...
እርሷ
ተው ብዬህ አልነበር
ይቅር ብዬ አልነበር
ነግሬህ አልነበር
ቃላት ፍቅር መሃል የሴት ቅስምን መስበር
ተው ብዬ አልነበር!!?
ይልቅስ ንገረኝ
እውነቱን አስረዳኝ
ተስፋ ቅስሜን ሰብረህ ጣለው
ፍቅር ልኬን ልክ አሳጣው
እንዴት ነበር
መተሳሰብ ...መተማመን
መፈቃቀር .....መከባበር
ቀልድ ሲሆን ልቦናህን የጀመረው ለማሻከር
እርሱ
....
ቡናውን ጨርሶ ሲነውን ልብ አለ
ያን ቀን የሚመስል ምስል አስተዋለ
ቡናው እድፍ መሃል
ተራራ ሚመስል
ቁልቁለት ሚመስል
ጭኗን የከፈተች ሴት ልጅ የምትመስል
ጥቁር ጭላጭ ስዕል
አየና ልብ አለ ......
የሆነ ቀን ምሽት ቀልቡን እንደጣለ፡፡
....



Scanned by CamScanner

## የምኘሻው– ፎሮ

ከመቅደሱ- ገባች…
ሳልሰመረ- ስለት
ሳልተሰማ - ጸሎት
-
ስለቷን አገባች… ምጽዋቷን ሰጠች
ፈጣሪ ዝም- ብሏል…
ጸሎቷን- ረስቷል
ጥያቂዋን- ንቋል…
ተስፋ- አልቆረጠችም
በሩን-ታንኳኳለች…
ያንድ-ቀን ተስፋዋን.. ዛሬም-ታሰማለች፡፡
ጸሎት- ታደርሳለች
ስ'ለት- ትሳላለች፡፡
ታዲያ…
ሴቲቱን- መች- ገባት - የአምላኳ ስራው
ባታውቀው- ነው'ንጂ… አንዳንዴም ፈጣሪው
እንደ-ሰው - ሁሉ
ሲፈሩት.. ጨካኝ.. ነው

## የአንድ ካፍቴሪያ ረዥም ትዝታ

ከሁለታችን መሀል ክብ ጠረጴዛ
በቆንጆ ሴት ልጅ ጣት ደረቱ እየወዛ
ከኔ ፊት ልጀቷ ፊት ለፊቷ እኔ
ፊቷ ማኪያቶ ጥቁር ቡና የኔ!!
እሽትሬይ
ካሽትሬ ጎን መጽሀፍ
እና መነጽርና ቁልፍ
ይታያል
(ከጠረጴዛው ላይ )
…..
ልጅቷ?
ዓይኑን ታየዋለች
እየተገረመች
እየተደነቀች
ልጁ
ዓይኗን ይሸሽዋል
ካይኗ ይከደናል፡፡
ልጅቷ
በልንጂ ንገረኝ እውነት ነው ? አለችው
ልጁ
ፀጉሩን እያሸ
ዓይኗን እየሸሸ
ምን ብዬ ልንገርሽ ምንድነው ሚባለው?
ዘጠኝ ሰዓት ያዩት ህልም ነው ሚመስለው
ለነገሩስ እውነት የሚያውቁት ውሸት ነው
…
ወሬውን አቋርጠ ….
ቡናውን ሲያነሳ ማኪያቶዋን ያዘች



Scanned by CamScanner

## ሙዚቃው

የነደደ ሽማ ግማሽ የቀለጠ
የአበባ ክምር ላንቺ የተሠጠ
በብርጭቆ ግማሽ ወይን የተቀዳ
ሮዝ የተቀባ የቤቱ ግድግዳ::
*
አንቺ የለበስሽው ረዥም ሃምራዊ
ከላይ የኔ ሸሚዝ ደማቅ ሰማያዊ
የቀለበትሽ ቀን
የቀለበቴ ቀን...
በጥቂት ወዳጆች ዙሪያችን ተከበን
ዝም ብለሽ ዝም ብዬ
ድሮን ለማስታወስ አንቺን ተከትዬ
ያለቃል ተግባብተን
ያለድምጽ አውርተን...
ሙዚቃው ትዝ ብሎን ወደ ኋላ ሄድን::
*
በስሱ ፈገግ አልሽ.. በአይኔ ጠቀስኩሽ
ልብሽ ያወራኝን በአይኔ መለስኩልሽ
ድንገት በዚህ መሃል...
አብራሽ የተማረች የጥንት ጓደኛሽ
ዝቅ ብላ በጆሮሽ.. ያልተሰማኝ ነገር ትንሽ አወራችሽ
በደማቅ ፈገግታ ዐይኖቿን እያየሽ?
እጅሽን አንስተሽ... ደረቷን መታሻት
እየሳቀች ሄደች...
ሰው መሀል ደመነች...

እኔ በበኩሌ...
እንዲህ ያለን ወሬ መተርጎም አልሻም
ምክንያቱም...
የስሜትን ሃሳብ 'ቃል መሃል' ሲፈልጉት አያምርም
ደስ አይልም::
*
ጎኔ ቁጭ ብለሽ ጎንሽ ቁጭ ብያለሁ



የመጀመሪያው ቀን
ከከተማ ወጥተን
በአንድ የሰማነውን ሙዚቃ አስባለሁ::
ሃሳቤ ዝግ ሲል
ካዳራሹ መሃል ወዳጅ ይሳሳቃል
ሙዚቃው ይጮሃል
*
ትንሿ እህትሽ
ወዲህ ወዲያ እያለች ህዝቡን ታዋራለች
ወንድምሽ ጥግ ላይ
ጓደኞቹ መሃል ትክዝ ብሎ ቆሟል
አውቃለሁ
ታውቂያለሽ
እህቱ ስትዳር÷ ወንድም ይከፋዋል
አባት ይከፋዋል
እናት ይከፋታል
ደግሞም...
እንዲህ ያለን ስሜት፡ሃጢአት እንዳይባል
ሰማይ ብራና ላይ... ፈጣሪ ጽፎታል
እንዲህ ሲል
"እናትና አባቱን.. የሰው ልጅ ይተዋል
ከወደደው ጋራ በአንድ ይተባበራል"
እና
ሄድኩኝ ወደኋላ
ሙዚቃ ፍለጋ..
ትዝታ ፍለጋ..
የመጀመሪያን ቀን ሁኔታ ለማየት ልቤ ተዘረጋ...
ነጩ ላይ ቁጭ ብለሽ
ነጩ ላይ ተኝቼ
አብረን የሰማነው ሙዚቃ ትዝ አለኝ
አብረን.. ያደመጥነው... በግራዬ ይገፔሽ.. በቀኝሽ አቅፌሽኝ
ትዝ አለኝ ሙዚቃው
ያኔ ያደመጥነው...
እነሆ ሙዚቃው



Scanned by CamScanner

## የፎኮጋ ህመም

እኒህ ገጣምያን
እኒህ ደራሲያ
እኒህ ሰዓሊያን...
ሶስቱ አማልክቶች
ረዳት ፈጣሮች
ሦስቴ ይስታሉ
ሦስቴ ይከዳሉ...
፩
ሃሳቡ ሳይመጣ እንጻፍ ይላሉ
፪
ሃሳቡ እንዲመጣ ሃሳብ ያስባሉ
፫
ሃሳቡ ሲመጣ ሃሳብ ይመርጣሉ
ትተው ይነሳሉ።
0

## የድሆች መጽናኛ

በአንዲት ትንሽ ሀገር
በአንዲት ደሃ ሀገር
ተስፋ በሌለባት
ዝነኛ ሰው ሲሞት ባልተጠበቀበት
ደስታ ነው ሚሆነው
ጥጋብ ነው ሚሆነው
በሀገሪቷ ሰዎች
በድሆች በሀብታሞች።
የሀገሪቷ ሰዎች ሁለት ሰበባቸው
ጥቂት ባለፀጎች...
ሊበሉ ሊጠጡ
ሊሰክሩ.. ሊዳሩ ሞት አይቀርም ብለው
ብዙዎች ድሆች ግን..
ፍጹሙ ደስታቸው
ዝነኛው በሞቱ ስለቀደማቸው።

Scanned by CamScanner

እርሷ
መናደድ ጀመረች
ድምጿን ከፍ አደረገች
እውነት ? ... ሆኗል ? አለች

እርሱ
ነግሬሽ ነበረ
አውርቼሽ ነበረ
እውነትን ሲያውቁት እውነቱ ይጠፋል
ምክንያቱም እውነት ...
የሚታወቅ ውሸት መሆን ይጀምራል
እናም
ንግግሯን ሳይሆን ድምጿን በጣም ፈርቶ
በቃ አትበሳጪ
በቃ አትናደጂ አሳት ተረጋግቶ
እርሷ
በትኩረት አየችው
በቁጣ አየችው
ብትወደውም እንኳ በመጠን ናቀችው
እናም
እንባዋ እያነቃት
ሣግ እየረበሻት
እንዴት
ለምን
እንዴት .....
ሳግ እየረበሻት !እንባዋ እያነቃት
እንዴት አልበሳጭ እንዴት አልናደድ
ተቃጥላ ባለቀች ሻማ ላይ ስትቀልድ
ለምን አልናደድ።
ብላው
ጥላው ወጣች
አይኖቿን እያሸች
....
ለሁለተኛ ግዜ
ከፊቱ ያለውን ሲኒውን ልብ አለ
ቡናው እድፍ መሃል
ተራራ ሚመስል
ገደል የሚመስል
ጥቁር ጭላጭ ስዕል
ጭኗን የከፈተች ሴት ልጅ የምትመስል
ምስል አስተዋለ
አየና ልብ አለ
የሆነ ቀን ምሽት ቀልቡን እንደጣለ።

•ለ ኢሽታር

## እምነት ክህደት እውነት

የምናምን ዕለት
ፀሐይ ትዞራለች
ባስራ-ሁለቱ መስኮት ገብታ ትወጣለች

.
የምንጠይቅ ወራት
መሬት ትዞራለች
ያማኙን ልቦና.. ሽፍታ ታደርጋለች

.
በገጣሚ ምናብ
ከንቱ የ'ምነት ዓይን ከንቱ ፍልስፍና
ሰማይ ነው የሚዞረው።...
ምክንያቱም..
የትላንቱን ኮከብ ከትላንቱ ቦታው
ዛሬ ላይ መች አየው?...

## ትዝታ...

እኔና ሃሳቤ...
ፊቴ ጥቁር ቡና...
ቡናው ጠረን መሃል ካንድ ትዝታ ጋር
ሥንት ነው ተዝታ?
ምንድን ነው ትዝታ?
ሰው ነው? ....ሥፍራ? .....ቦታ
ምንድን ነው ትዝታ።
*
ምን ነበር ሁኔታው
ልኖረው ሥጀምር...
ጊዜ ፍጥነት መሃል.. ትውሥታ የሆነው
ትዝታ... ምንድን ነው?...
ዘፈን ነው ቀረርቶ
የራሥ መደለያ የሃሰት ቀበቶ
ምንድን ነው ትዝታ
ትውስታ እንዳይባል.. ራስ ሊሸነገል
ፀፀት እንዳይባል..
ጊዜ ሊያሸንፍ ነው.. የራስ ክብር ሊጣል
ሣይኖሩ ማስታወስ ኋላ ዕድሜን መናፈቅ
መናፈቅ...
መናፈቅ...
ባሣብ ወደኋላ ..ራስን ማንፏቀቅ
* * *
ይመሥለኛል እኔን..
ከጠረጴዛው ላይ ቁጭ ብዬ ማየውን..
ባሣብ የተረሣ..
ቀዝቀዝ ያለ ቡና.. ተቀድቶ የቆየ
ጭላጭ የጉደር ወይን.. ፊቴ.. የነበረ
ንፁህ የምንጭ ውሃ መድረቅ የጀመረ
ጥውልግ ፅጌሬዳ የተሠባበረ
ይመሥለኛል እኔን..
ከጠረጴዛው ላይ ..ቁጭ ብሎ ማየውን..
* * *

"ከዋክብት አረግፈው እግርሽ ስር ይውደቁ
ሮዝና ጀዝሚን ሊሊና ሳሮኖች በፊትሽ ይሳቁ
ፀሐይ ስትበረታ ፊትሽን ሊከልል
ከአናትሽ በላይ ተራራው ከፍ ይበል።

ልሥልስ አረንጓዴ...
ህይወት ያለው ቅጠል
ይዘርገፍ መሬት ላይ ዙሪያሽን ይከበበው
ለወገኞች እንጂ...
ለእንዳንቺ ዐይነት ሴት ቀይ ምንጣፍ ምንድነው?
በምን ምክንያት ቢሉ
በምን ምክንያት ቢባል
ከተፈጥሮ በላይ ገዥ እንዲሆን ልዑል
የሰው ልጅ ለክብር ጥንቱንም ተሰርቷል።"
ይህ ነበር ሁኔታው
ይህ ነበር ሙዚቃው
ፍቅርን ስንጀምር ለሁለት የሰማነው...

## ጊዜ

እግዜር
በምድራችን የተከላት
ጊዜ የሚሏት- ጽጌረዳ
ገና እንኳን ሳታብብ ገና ሳትፈነዳ
ጨለማዋ እሾህ
ጨክኖ ቢወጋት
ወግቶ ቢያሸንፋት
የልቧን አወራች
እውነት ተናገረች...
ነገ በማለዳ... ዛሬ ሟች ነኝ አለች።

ቁም ነገራችን ላይ ፈገግ እያለብን
ሌሊት የፃፈውን ግጥሙን ሲያሰማን
ርዕሱን ነገረን
"ብቻዬን ነኝ" አለን።

ብቸኝነት...
-
ግራጫ ነፍሳችን ክንፏን ሊሰባብር
ወተቱን ሳንጨርስ አጥንት እንድንሰብር
የሀሳብ ዙፋኑን ይዘረጋው ጀመር...
ብቻዬን ነኝ አለን....
እኛን ግን ጨነቀን ዕልፍ ሰው መሰለን
ክንፉ ተለቀብን
ከበደን ጨነቀን
ብቻዬን ነኝ ሲለን ሁለት ሀሳብ ገባን
አንድ...

አንደኛ የናቀን
እኛን ያገለለን...ሰነፎች የሚለን
መሰለን።
ሁለት...

ሁለት ያወቀብን
ክፋት ተንኮላችን
አድማ መምታታችን
መግደል ቢያቅተን ማግለል መቻላችን
ስም ማጥፋታችንን
ያወቀብን መስሎን
"ብቻዬን ነኝ" ሲለን
በጣም ደነገጥን
ከእኛ መካካል...
እንደኛ ሚያስበው
እኛኑ.. ሚመስለው
አንድ አይነት የሆነው
ጭቅጭቅ አማረው



ግጥሙን አቋረጠው
"እኛ ምልህ?" አለው...
*
ብቻዬን ነኝ ያለው የፌዝ ሳቅ አሳየው
*
ሲጋራውን ጥሎ በ'ግሩ እየረገጠ
ለአስተናጋጇ የቡናውን ስኒ በ'ጁ እየሰጠ
ከጨቅጫቃው ወጣት..
ስጋ ቅብ ግንባር ላይ ባይኑ እንዳፈጠጠ
ምላሽ ይሰጥ ጀመር...
-
"የግጥም ሞት ሌላ....
ዓለም ሀሳብ ሆና ሀሳብ የጠፋ 'ለት
ከቃላት ከፊደል የተሟገቱ'ለት
ባልተሰጠ መክሊት እናትርፍ ያሉ ለት
የግጥም ሞት ይሄ መቼ ብቸኝነት።
እያለ ሲያወራ...
የጨቅጫቃው ወጣት...
ዓይኑ ወለቀበት
ምላሱ ረዘመ ..ከከንፈሩ አልፎ መሬቱን ነካበት።...
ብቻዬን ነኝ ያለው?...
ለዚህ ለአንድ አይነት
በጣም አዘነለት።...
እናም
ከውዳቂ አፈር ዓይኖቹን አንስቶ
በልቦናው ዕንባ አቧራውን አሽቶ
የነትራካው ወጣት...
ወላቂ አይኖቹ እስኪደርቁ ድረስ
ደሞ ሌላ ጥበብ
ደሞ ሌላ ሀሳብ
እስቲ ስሙ እያለ
በውብ ቃላቶቹ ልብ እያማለለ
የእኛን የልጅ ሀሳብ ወዲያ እያቃለለ
ደሞ ሌላ ቡና ድገሚኝ እያለ
ሳልሳይ ትንባሆውን እያቀጣጠለ



Scanned by CamScanner

ንፁህ ምንጭ የነበር
አበባ የነበር
ከዕንፋሎቱ ጋር ይፋጅ የነበረ አቦል ትኩስ ቡና
እና..?..
ቡናው ቀጠነና..
ወይኑም ተጠጥቶ ሩቡ ቀረና
ንፁሁ የምንጭ ውሃ አሸዋው ታየና
ዛሬ...እዚያ ካፌ
ዘወትር ካለሁበት ..ጠዋት አራት ሠዓት
እኔና ሃሳቤ... ፊቴ ጥቁር ቡና
እነደ ትላንትና..
ቡናው ጠረን መሃል ከአንድ ትዝታ ጋር
ይህ ግጥም ተፅፏል
የህይወትን ቀለም ሣላየው ወይ ሳልኖር
ትዝታ ምንድ ነው...

# ብቸኝነት

"ተረት...ተረት"
"የመሠረት"
"ከነርሡ ጋር ሆኖ ብቻውን የሆነ
የተመሰገነ
እጅግ የገነነ
አንድ ወጣት ነበረ..."
"እሺ...!"
ተረት ተረት
የላም በረት
አንድ ዐይነት ሚያስቡ
አንድ ላይ ሚያስቡ
አንድ ላይ ሚራቡ
አንድ ላይ ሚጠግቡ
ለመብረር ያልቻሉ.. በልብ የሚሳቡ
ትንሽ ሲጠበቡ
እጅግ የሚጠቡ
አስሩ ነበሩ...
"እሺ.."
አንድ ቀን
የተመሰገነው
እጅግ የገነነው
የሰው ልጅ በሙሉ የ'ውነት ሰው የሚመስለው
አንድ ቀን ሌሊት ላይ
ከጨረቃ ጋራ እየተማከረ
ከከዋክብት ጋራ....ባንድ እየዘመረ
'ብቸኝነት' የሚል መጠርያ የያዘ ...አንድ ግጥም ፃፈ
እናም
በውበቱ ይሁን ወይም በመልክቱ
አስሩ አኮረፉ
አስሩ ተከፉ
በዓይኖቹ ትኩረት ነፍስ እያስተዋለ
ትምባሆ አውጥቶ እያቀጣጠለ
ከቡናው አንስቶ ጥቂት ፉት እንዳለ...

እደግመዋለሁ…
'የግጥም ሞት ሌላ…
ጥራዝ ነጠቅ ወሬ
ተፅፏል ስንባል በብጣሽ ወረቀት በበጎች ብራና
ይልቅ ልንገራቹ…
ሕይወት ያለው ግጥም ታትሞ ይኖራል በሰዎች ልቦና'…
የግጥም ሞት ድፍረት
አንዴ የፃፉትን ሺህ ጊዜ ሲያነቡት
መቼ ብቸኝነት
ብቸኝነት ህይወት….
ግጥም መወለጃው…የምክንያት እናት
የግጥም ሞት ሌላ…
ዓለም ሃሳብ ሆና ሀሳብ የጠፋለት
ከቃላት ከፊደል የሚሟገቱለት
መቼ ብቸኝነት?
ብቸኝነት…?
ብቸኝነት ሕይወት
-
ግጥሙን ጨረሠ።…
ምላሰ ረጅሙ ሊሟገት ከጀለው
ቁጣ ባዘለ ድምፅ ብቻዬን ነኝ ያለው.. ወሬውን አስቆመው
በመንፈስ በሀሳብ ድንግል ሆኖ ታየው
እናም…
ያለመኖር ያህል በቃል ፍቅር ናቀው።
መሬት አጎንብሶ…
ጆሮ እና ዓይኖቹን ቢፈልግ አጣቸው
እናም…
ከጨቅጫቃው ጋራ
እኛንም ባንድነት ጸሎት አስተማረን

አቤቱ…
የብቸኝነትን ጣዕም አሳየን
ምክንያቱም
መንጋ ሆነን የምንኖር አዲስ ሃሳብ የራበን ነን።
አቤቱ
ዓይናችንን መልስልን
ምክንያቱም
በአበቦች ልብ ላይ እሾህ በትነናል
የበተነው እሾህ እኛኑ ወግቶናል
ግና ክፋታችን የወጋንን እሾህ ከእግራችን ሳንነቅል
እርሱን ወግቶታል ወይ ብለን ጠይቀናል
በዚህም አፍረናል
ስለ ፍቅር ፅፈን ፍቅርን እረግጠናል
ላሳብ ለቃላችን ባዳዎች ሆነናል
አቤቱ ይቅር በል።
አቤቱ…
ማን እንደሰረገ አናውቅም…
በዘፈኑበት ግን እንደንሳለን
ማን እንደሞተም አንጠይቅም
ሙሾ ሰማን ብለን ማልቀስ እንወዳለን
እናም…በዚህ ታላቅ ስህተት
በዚህ ታላቅ ቅጣት
በመንጋ እይታችን ዓይናችን አጥተናል
ከነመፈጠሩም ጆሯችን ደንቁሯል
ባለማስተዋልም…
በበደሉ ምክንያት በፈጣሪ ሚዛን
ለፈጣሪው ዓይን
ለንቀት የሆነ ሕዝብን እንመስላለን።
እናም ጌታችን ሆይ
አንድነትን ሳይሆን
አንድነትን ሳይሆን
አንድ መሆን አስተምረን
አሜን…!!!

## ወቅቶች

ነፋሳት ላይ ቆሜ
ነፍስ ባጣ ዕድሜ..
ከርሜ
ከርሜ
ነፍስ ግዛ ቢሉኝ
እሣትን ጨበጥኩኝ
ከቶኑ ገባሁኝ
እሣቱ ባይፈጀኝ.. እሣቱ ባይሞቀኝ
እሣቱን ዘልዬ.. ከውሃው ገባሁኝ
ከውሃው ጠለቅኩኝ።...
ከውሃው ጠልቄ..
ውሃው ተዘፍቄ...
ወደ ኋላ ዞሬ.. በ'ሣት ተቆጨሁኝ
በ'ሣት ተናደድኩኝ
መሬትን እንዳላይ ሥላላቃጠለኝ።

## አንድ ሰው

እሁድ ማለዳ ላይ..
ገላዋን ታጠበች
ልብሦቿን ሰበሠች
ሸቶ ተርከፍክፋ ከጎዳና ወጣች።...
በመንገድ ስትጓዝ...
የፀጉሯን መዘናፈል የጡቷን መኮፈስ
የረጨችው ሽቶ ካደባባይ ሲነፍስ
እሷን ያየ ሁሉ ወንዱ ተጨነቀ
በደም በውበቷ እየተደነቀ
ያስተዋላት ሁሉ ዓይኑ መንገድ ሣተ
ከዳሌ ከጡቷ ሔደ ተከተተ።...
(ከቦታው ደረሠች።)...
* * *

ወዳጇ አልመጣም
ሠዓት አልጠበቀም
ለውበት አልሣሣም።...
ሠዓት ገላመጠች
ፊት ኋላዋን ቃኘች
ማኪያቶ ደገመች
ዙሪያዋ ባለው ሰው እጅግ ተናደደች
እልህ ልቧ ሞላ
ፊቷ ከደም ቀላ
የሚመኛት ሁሉም።... ወንዶቹ በሞላ
የርሷ ልቧ ሌላ።...
ሠዓቱ ረፈደ
የጠዋት ደስታዋ ከዕርሷ ተሠደደ
* * *

አይኖቿ ረጠቡ
አንድ ሠው አሰቡ
አንድ ሰው ተራቡ።...
አንድ ሰው ነበረ እርሷን የናፈቀው
ያን ያልመጣውን ሰው።..
ናፈቀው።!!!

Scanned by CamScanner

## ፍለጋ

የፍለጋ መንገዳችን
የእውቀታችን አጭር አጥር
እኛን
እኛን ባጭር… እንዳያስቀር
አምላክ ባ'ለም- ባይኖር እንኳ…
ሕይወታችን መልካም ሆኖ.. ጎዳናችን እንዲሰምር
ራሳችን.. ለራሳችን…
እግዚአብሔርን.. እስኪ እንፍጠር

## ወንድ ሎሌት ከሴት ልጅ ፊት

የሴት ክናድ ተንተርሶ
ጡት ከንፈሯን ባፉ ጎርሶ
በ'ጆቹ ጣት ፀጉሯን ምሶ…
-
ከግርግር ተገልሎ
ከደረቷ ለጠፍ ብሎ
ወላፈኑን ጭኗ ተፋቶ ከስሜት ምጥ ሲገላገል
ወንድ ልጅ ሴት ፊት ነው… የቀን ግፉ ቀለል የሚል
ግራ ቀኙን የሚያስተውል።
-
ያላወሩት በደል ፀፀት እንዳያከም
ያልተሠማ ለቅሶ እርምን እንዳይፈፀም
የወንድ ልጅ እምባም ለብቻው አይፈስም..
ወንድ ልጅ ብቻውን ፍፁም አያለቅስም
እንደ ትንሽ እድሜው እንደ ልጅነቱ
ሆድ ሲብሰው
እንባ ሲያንቀው
ለኔ.. እንድትል ውድ እናቱ

በእናቱ ምትክ ግራ ጎኑን አቅፎ
ጡቷ መሃል ተወትፎ
ደረቷ ላይ ተለጥፎ
አንገቷ ስር ተደግፎ
ትከሻዋ ዙሪያ እጆቹን ቆልፎ
ያን ጊዜ ነው የወንድ ልጅ እንባው
የቀን ምጡን..የሚተፋው።
ትከሻውን እንዲቀለው ተስፋን ይዞ እንዲወለድ
ጭንቅ ምጡ እንዲወገድ
ለብቻው አይደለም ወንድ ልጅ ሚያነባ
ሴት ልጅ ሥታቅፈው ነው ሆዱ የሚባባ።

ግፍ ቢሠራም
ፀፀት በላኝ አትለይኝ ብሎ

Scanned by CamScanner

፬
ዓለሙም ዕብድ ነው
ግና ያ'ለም ዕብደት ካንተ የሚለየው...
አንተ የምታብደው ለዓለም ስትል ነው...
ዓለሙ ያበደው አንተን ሊሳብድ ነው።
ወገን ተሰቃየን
አውቆ የሚተኛ አቋመ ቢስ መሀል...
ለብቻችን ነቅተን።



# ውበት ከመታመም

እቴጌ ጣይቱ
ጃዛ'ምባ ካለበት
መሀል አራዳ ነኝ
ሙዚቃ ላዳምጥ ቢራ እየጠጣሁኝ
.....
ብቻዬን ሰው መሀል
ሙዚቃ መካከል ራስ ለመሸንገል
ከማይረቡ ሰዎች የወሬ ደመና.. እራስን ለማግለል
በጊዮርጊስ ጠበል
ልብን ለመደለል
.....
ድው...
ግም
ድው...
ግም
የድራመር ግጥም
(ሙዚቃው ጀመረ)
....
ኪዉ...
ኪል
ኪው...
ኪል
የሊድ የቤዝ ፊደል
(ሙዚቃው ጀመረ)
ዋይ....
እምቧ...
ዋይ
እምቧ...
ዋይ..
እምቧ
የእስትንፋስ ሥዕል
ሙዚቃው ጀመረ።...

ሴቲቱን አስምሎ
ቢበደልም..
አንቺ አለሽልኝ ፍቅርሽ ይበቃኛል እካሣለሁ ብሎ
በለስ ፍቅርን ተቀብሎ
አይችሉት ጉድ አብሮ ችሎ...
...ከስሜት ምጥ ሲገላገል...
ግራ ቀኙን ልብ ብሎ .. ክፉ ደጉን ሲያስተውል
ወንድ ሴሲት ሚስቱ ፊት ነው ከሃዘን መለሥ የሚል
እናም አባት..
እናም ሎሬት..
የልብ ላይ እሣት ብቻውን ከፋመ
ያላወሩት በደል ፀፀት ካላከመ
ያልጮኹበት ለቅሶም እርምን ካልፈፀመ
ስተት ነው
በደል ነው
የወንድ ልጅ እንባም ለብቻው አይደለም
ወንድ ልጅ ብቻውን ፍፁም አያለቅስም
በፍፁም
በፍፁም ...

# ክሩት ክደነት እብዱት....

፩
ብቸኝነት ብርዱ ገላህን ቀዝቅዞ
ከሰው መሐል አንተን ለብቻህ ሰቅዞ
መጠየቅ ሥትጀምር...
ለምን?.....እንዴት?....ሥትል?....
ጥያቄህ በራሱ እብደት ነው የሚባል
ኡፍ...
አቋመ ቢስ መሀል ለብቻችን ነቅተን
አቦ ተሰቃየን
-
፪
መጠየቅ ስልችቶህ ከሕዝቦች ስትርቅ
በራስህ ዓለም ላይ ሕሊናህ ሲራቀቅ
አይህ ዝም ባለ
እብድ-መባል አለ
ኤጭ...
አቋመ ቢስ መሀል ለብቻችን ነቅተን
አቦ ተሰቃየን።
.....
፫
የሕዝብ ሁሉ ሀሳብ የእብደት ሲመስልህ
ያንተ ሀሳብ የውነት...
እውነት እንደሆነ ውስጥህን ሲሰማህ
በገዛ ሀሳብህ...
ዕብዱ ትባላለህ።
ኤድያ...
አውቆ የሚተኛ ሕዝብ መሀል ቆመን
አቦ ተሰቃየን።

Scanned by CamScanner

ከታላቅ ውድቀቶች..ከ'ነዚህ መካከል
ጻድቅ ሰው ይገኛል።
እናም…
ሠባቴ ቢጥሉት ሠባቴ ይነሳል
ሥለዚህ….
እባክህ…….
ድራም ልቡን ምታው
አናቱን ኮርኩመው….
ለጊታር ለሲዱ…
በተነካ ቁጥር 'ኪው' 'ኪል' ለሚለው
ለፍሉት ለሳክሱ…
እፍ ባሉት ቁጥር…'ዋይ' 'እምቧ' ለሚለው
ድራሙ ልብ ነው…
ድራሙ ሕይወት ነው…
ሥለዚህ ሕይወትን መሐል ልቡን በለው
በለው
በለው
በለው…
ግራ'ጅህ አይድከም ቀኝ እጅህ አይቦዝን
ከውድቀት ከዕንቅልፍ
እንደምትገኝ…ሕልም
ውበትን ታያለህ….ተወልዳ ከሕመም…
ባክህ ባለ ድራም…………"
…………………



## የወንዝ ፍቅር

ተነስቷል..
ግን
ደርሷል።
አጋምሷል ፈጥሟል
እንደገናም ደግሞ…
ከተነሳበት ላይ መጓዝ ይጀምራል…
ወንዝ ጉዞው መች ይቆማል?
ወንዝ ጉዞው መቼ ያልቃል?
ዳንሠኛ እንዳልነበር..
በተራሮች መሃል ዳንግላሳ ሲዘል
ሲጓዝ እንዳልነበር…
ድንጋይ ላይ ለመውደቅ ከድንጋይ ላይ ሲዘል
ይኸው እዚህ ደግሞ…
ከባሕር ማሕፀን በጀርባው ተኝቷል…
ወንዝ ጉዞው መቼ ያልቃል
ወንዝ ፍቅሩ መች ይቆማል?......
.......
መቼም ለተጓዡ ቋሚ ፍቅር የለውም
መንገደኛ ፍቅሩ በየሄደበት ነው።
ከመጀመር በቀር ፍፃሜ የሌለው
መንገደኛ ፍቅሩ ዘወትር አዲስ ነው…
ወንዙ…
ለጥ ያለ ሜዳ ላይ አበቦች አፍቅሯል
በጥምዝ እጆቹ ተራሮችን አቅፏል
ሸለቆውን ስሞ ከባሕር ተኝቷል።
የዚህ ወንዝ ፍቅር…
በየደረሰበት የ'ውነት ያፈቀረው
ውበት የወደደው
አበቦች የሳሙት አበቦች የሳመው
በተራሮች መሐል
ዳንግላሳ ሂዘል..ሲደንስ የዋለው
ውቅያኖስ አልጋ ላይ…
በጀርባው ተኝቶ የተሸኮረመመው።



Scanned by CamScanner

የሙዚቃ ስሜት ምንነት ያልገባው
መንፈራገጥ ይሏል አንዳንዱ ተራ ሰው

.....
በስተቀኝ ጥግ ላይ....
የተቀመጠው ሰው
ዐይኖቹን ጨፍኗል... ተመስጦ እንደያዘው

....
አብዛኛው ሕዝብ ግን....
የዞትር ጸሎቱን...
መልከዐ ጊዮርጊስ በ'ጁ እንደጨበጠ
ከሥጋው..ከፍ ብሏል..እንደተቀመጠ

...
ያ የቅድሙ ሰው
ሙዚቃ ለመስማት
ሠው መሃል ብቻውን ተቀምጧል ያልነው
ሙዚቃው... ሞቅ ሲል
ሙዚቃው.. ሲደራ...
ከተቀመጠበት በርጋታ ተነስቶ...
በጫጫታው መሃል እንዲህ.. ብሎ አወራ::...
"ሠውዬው...

ማነህ ባለድራም...
እርገጠው የታቹን
በለው ድራምህን
ቀኝ እጅህ አይድከም ግራ'ጅህ አይቦዝን
ጥቂት ብቻ ታገስ...
ከስቃይ 'ሚወጣ ታያለህ ውበትን::"
ድው...
ግም...
ድው...
ግም...
የድራመር ግጥም...
ለውበት መታመም... ዉበትን ማሳመም::
"ባክህ ባለ ድራም...
ምትመታው ከበሮ..ትክሻዬን መስሎኝ....
ምትመታው ከበሮ የ'ኔን ወገብ መሥሎኝ...
እጅግ አሳዘነኝ
ዕንባ ዐይኔን አነቀኝ....
ቢሆንም ...
ቢሆንም...
ግው....
ድም...
ግው..
ድም..
የድራመር ግጥም..
በፍፁም አይቆምም::...
የድራመር ግጥም ግራ.... ቀኝ.... መመታት
ከትክሻ መዝመም በተንኮል መቀጣት
የኔን ሕይወት አይነት::
እናም እባክህን...
በለው ከበሮህን...
ቀጥቅጥ ግራ ቀኙን ቅኝቱን እንዳይስት እርገጠው እግሮቹን...
ሠካራም ይደንስ...
የከበሮውን ልብ ጨከን ብለህ ምታው
የዳንሡን አዳራሽ...
በብራናው ጬኸት 'ዋይ' 'እሪ' አሰኘው
ድው አድርገው
ግም አድርገው
ቀኝ እጅህ አይድከም ግራ'ጅህ አይቦዝን
ጥቂት ሰዓት ታገስ...
ከሕመም ተወልዳ ታያለህ ውበትን።
እናም እባክህን....
ረፍት እንዳታደርግ...
በስልት የተቃኘ...የረቀቀ ተንኮል ሚመስል ሥራህን
ቀጥል ድብደባህን::
ባታውቀው ነው 'ንጂ...
ውብ የድራም ግጥም..ሕይወቴን ይመስላል
ምትመታው ከበሮ እኔን ይወክላል
ምክንያቱም...
ከብዙ መመታት... ከብዙ መገለል

ተስፋ ከቆረጠ ገጣሚ ወይም /ግለሰብ/ ብቻ ነው
ብለህ ከምትከኝ...
ውሸታም ነህ ብዬ ..እሞግትሃለሁ
አልያም...
አልያም...
የውሸት ታሪክ... ማከማቻ ቅርጫት ብዬ እተችሃለሁ።
•
ጥቂት ዝግ ብለህ
ቀልብህን ሰብስበህ
ከዓይንህ ፊት ያለውን.. ታሪክ ልብ በለው
ደግሞም ዘፈን መሃል..
ጆሮህን የሞላው አዝማች አስተውለው
ቴዎድሮስ
ቴዎድሮስ
የቋራው .. የቋራው.. የቋራው የሚል ነው..
እንግዲህ...
እራስን በራስ እጅ ገድሎ መሰናበት
እንዳ'ንተ ከሆነ...
የተራ ገጣሚ የቃል ጨዋታ ነው
እንደ'ኔ ከሆነ...
በሽንፈት ማሸነፍ.. የሚባል..'እውነት' ነው
ግን ..
ይህ ሁሉ ቢሆንም...
እኔ .. ግን .. አልሞትም!! ...
*
ምክንያቱም...
ምክንያቱም?...
*
ምክንያቴ ምክያትህ መሆን ስለማይችል
በዚህ ስንኝ መሃል
የዚህን ውብ ግጥም ሃሳብ እንጠቅልል

Scanned by CamScanner

## ስንዱ ዘርፉ እብቅ ዘጋኝ

የርሱን ቃል አድምጦ
በርሱ ቃል ተመስጦ

ሙዚቃውን ነስቶ
ቀረርቶውን ሽቶ
መፈክሩን ሰምቶ
ቁጥር የሌለው ህዝብ ስለስሙ ሙቷል
ለስሙ ተጋድሏል
አላማውን ይዟል
መፈክር አንግቧል..

እሱ 'ቴ' ምን ተዳው
ምን ተዳው
ምን ተዳው...

ያለፈን እረስቷል
አላማውን ስቷል
መፈክሩን ጥሏል
ህይወቱን ቀይሯል
በጎርደን በውስኪ በተሚሽ አፉ ቀልድ ፌዝ ጀምሯል
ይሄ የውሻ ልጅ...
መቼ የሰው ሕይወት ያለፈ መስሎታል

## ፍርሃት

*

ድንገት በመንገድ ላይ..
አንድ የሆነ ስፍራ የልብ ምት መቆም
የሕይወት መፈጸም..
ድንጋጤን ያዘለ..
የሆነ ሁኔታ... ድንገት ይሰማሃል..
ድምጹን ካደመጥከው
የሕይወት ምንነት በዓይንህ ፊት ይጎድላል
የህይወት ርምጃም ከዓይን ጥቅሻ ፈጥኗል!!..
ያን ጊዜ..
ሰው መሆንም ያንሳል...
እናም
ያ
እጅጉን አድርጎ ያስደነግጥሃል!!!!!
ለምን? ... ብትል ---
ታላላቅ ህልሞችህ...
ቅዠት እንደሆኑ ውስጥህ ይነግርሃል።......
*   *   *
(መኖር ግን መልካም ነው)
ምክያቱም...
ያንን ባሰብክበት ቅጽበቶች መሃል
ባለመኖር እንቅልፍ እልፍ ሰው ተሸኝቷል
እልፍ ሰው ተኝቷል
*
ሰግተህ ላታመልጠው
ስለዚህ መሞት ነው
ምክንያቱም
ፍርሃትም በራሱ
ከመሞት የሚልቅ ታላቅ የሞት ሞት ነው!!...
ስለዚህ... መሞት ነው!!

(ማሰሪያ አንቀጽ)
እንዲህ ያለ ግጥም ሊፃፍ የሚችለው

Scanned by CamScanner

ተራሮች ያቀፈው
አበቦች የሣመው
ሸለቆ የገባው...
የማንንም ሕይወት በምስጢር ያዘለው
ወንዙ.
ይኸው....
ሌላ ፍቅር ያዘው
ከመሬት ተስማምቶ ከባህር ተኝቶ እንዳላስተዋልነው
ወንዙ...
ይኸው ምንም ሆኖ መንገዱን ጀመረው
ፀሀይን ለማቀፍ
ፀሀይን ለመሳም...
ከባህር ተነሣ.. ምንም..መስሎ ምንም
ወንዝ ፍቅሩ መች ይቆማል
ወንዝ ፍቅሩ መቼ ያልቃል?......

## ዝና

እንደልጆች ዘመን
እንዳሁን ከሆነ ጀግና 'ሚመረጠው?
ዝነኛ ሚሰኘው..
የአባቶች ጀግንነት ዝናቸው በሙሉ 'ያልተመረጡት' ነው።!!!

Scanned by CamScanner

ሳንድ ዝግባ ሲባል
እልፍ አበባ መቁረጥ እልፍ አበባ መጣል
ማስተዋል ቢመስለን
ባለማወቅ ነው እንጅ
ያለማወቅ እውቀት ስልጣኔ መስሎን
ልማት ነው እያልን የሙጥኝ ስላልን
እንጂ...
ብናውቀው ኖሮማ ውበት ቅርስ እንደሆን...
ብናውቀው ኖሮማ..
በህይወት ግምጃ ቤት.. ተጥሎ የሚኖር ተምሳሌት እንደሆን
ብናውቀው ኖሮማ
በውበት ብናምን ቅርስን ብናከብር
ያን ያህል ጨክኖ ይህን የርሷን መንደር
ይህን የእርሷን ሰፈር
ማን ያፈርሰው ነበር።...

ዛሬ...
በዚያ መንደር
ከልጅት መኖሪያ ፍርስራሽ ጣውላ ስር
ከቤተ-መንግስቱ አረንጓዴ ሰፈር
ከፉ ጠረን ይዞ ነፋስ ይጓዝ ነበር።





# ሁለት ፍቅር

ሳሚኝ በከንፈርሽ እስከ ሞት ጫፍ ድረስ
ሲያል ይሁን ቤቴ መኖር ቅጽሩ ይፍረስ
መች ይቀራል ስጋ ፈርሶ ከመበስበስ።
አንድ ክንፌን ፍቅር ይዞት
አንድ ክንፌን ቅኔ ጠሞቶት
ጉድ ሆንኩልሽ
ሁለት ፍቅር ግራ አጋባኝ
ሁለት ፍቅር መላ አሳጣኝ
እኔን ከኔ ነጣጠለኝ።
ለማን ልሁን ከየት ልደር
የት ለማረፍ ወዴት ልብረር
ያለ ፍቅር ቅኔ ላይሰምር
ያለ ቅኔ ፍቅር ላይኖር
ክንፌ ተሰብሮብኝ
መድረሻው ጠፍቶብኝ
አንድ ሌሊት እንዳሰበኩኝ ?
አንዲት ፍጽምት ቅድስት ሃሳብ ወረቀት ላይ መጣችልኝ
አሁን አብርሆት ነው ብቅ በይ ወደ እኔ
ምክንያቱም
አንቺን መርጫለሁ ከድርሰት ከቅኔ
እናም ብቅ ብለሽ
ሳሚኝ በከንፈርሽ እስከ ሞት ጫፍ ድረስ
ሲኦል ይሁን ቤቴ መኖር ቅጽሩ ይፍረስ
መች ይቀራል  ስጋ ፈርሶ ከመበስበስ
ስለ ሴት እንደሆን
ነገስታት ደክመዋል
ሃያላን ወድቀዋል
ንፁሃን ስተዋል



Scanned by CamScanner

ጦር የወደቀበት
በተራ ወታደር የተረታ ንጉሥ የሚመስል አይነት፡፡
ሞቱን የሚጠብቅ
ታስሮ የሚማቅቅ
መሞት አለመሞት  የኑሮ ትንቅንቅ
እሷ መንደር መሃል ይታያል ይሄ ሃቅ፡፡

የፈረሱ መልኮች
የገጠጡ ገጾች … የወየቡ እጆች… ያፈጠጡ አይኖች
የጠቆሩ ቀዮች
ወገ፡ አልባ ጥቁሮች
ቆዳውን የበላ እረገኘርም አጥንት
ብዙዎች የሞሉበት
ሞልተው ሚሞቱበት
ከሕይወት ተፋተው በተስፋ እጦት ምክንያት፡፡
ሕዝቡ ሚደርበው
ነጠላና ጋቢው
ሀዘን የሸመነው ጨለማ ብርድልብስ
ግራ ጎረቤቷ ህጻን የሚያለቅስ
እናቱ የሞተች በዐዋላጅ እጦት፡፡
የቅኝ ጎረቤቷ እናት ምታቃስት
ሴት ልጇ ያበደች የምታስታምማት፡፡
እወዲያ ጥግ ላይ…
ቤት አልባ ጎልማሳ
በረሃብ ምክንያት.. አካሉ የከሳ
ከዘመናት በፊት…
በሺህ ዘጠኝ መቶ .. ዘጠና ሁለት ዓመት
ሁለት አይኑን ያጣ ..በወንድሞቹ ቀስት..
ወዲህ ከትበው ጎን
ያገሩ ቆሻሻ በሚያልፍበት በኩል
መምጫው ያልታወቀ… አንድ ትንሽ ህጻን..
እድሜው የሚመጥን አስር ዓመት ያህል
የሰውና የከብት ቆሻሻ ካለበት
ትቡ ጎንሚተኛ
በልጅነት እድሜው የሌሉት ወላጆች

# የፈረሱ መልኮች

ከዘመናት ኋላ
ድንገት ባጋጣሚ አንድ ቀን ያየኋት
እሷን እያሰብኩኝ
በበራቸው በኩል ትላንትና አለፍኩኝ፡፡
ገረመኝ
ደነቀኝ ...
ለካ ..
ስፍራቸውን ለቀው
ቤተሰቡ ሁሉ ከዚያ ቦታ ጠፍቷል
ኮረብታው ላይ ያለው መኖሪያቸው ግና...
ግድግዳና ጣሪያ አጥሩ ፈራርሶ ወለሉ ይታያል
እኔ በበኩሌ... ከዚህ የበለጠ ላወራ ምችለው
አንድም ቃል የለኝም
ፈርሶ ለማየው ቤት አራት ኪሎ ላለው
ሁኔታው ...

ክፍት የእንጨት አጥር
ትንሽ ገደድ ያለ... ልሙጥ ቆርቆሮ በር
መላ ቅጥ የሌለው
ለቅሶና ሙዚቃው የማይለይ ሰፈር
ነበር ...
ግን...
ፈገግታ የሞላው
በቤቱ ጥበት ልክ... ደስታ የማያጣው
ግድግዳውን የሚያልፍ ሃዘን የወረረው
ላ'መት በዓልና
ላ'መት በዓል ዋዜማ ብቸኛ ቀናቸው
እፎይ የሚሉበት
ህጻናት ተጫውተው
ጠግበው የሚያድሩበት አዋቂዎች በልተው
ሰፈር...
እዚያ ነበር፡፡
አሁን ግን የለችም

## ፀሎተ ቶማስ

ይህን እናምናለን...
ምስጋናና ትዝብት እየተቀበለ
የሰው ልጅ ፈጣሪ በሰማያት አለ፡፡

በዚህ መናፍቅ ነኝ
ልክ እንደ ፈጣሪ መፍጠር እየቻለ
ብቻውን የሚኖር ያልፈጠረ እንዳለ፡፡

Scanned by CamScanner

ባይናችን እያየን
እያወቅን ፈርተን የገባን ያልገባን
በራሪ ወፎች ነን!!
ፍፃሜውን አውቀን ተውኔቱን የናቅን
----
ምን ነካው ሼክስፒር
እኛ ማለት እኮ???
እኮ ?

## ሁለንተናዊነት

በሁለተናዊነት አሳቢ ላይ ሆኜ
በቀድሞነት ህይወት...
እርሷን ተማፅኜ
ደግሞም..ላሁንነት.. አንቺ ላይ ተግኜ
'ምን' መሆንን ሳስብ
'ምን' መሆን ገለባ
'ምንምን' ሳስበው
'ምንም' ፍሬ አልባ
'ምን' አቦ 'ምንምን' በአንድነት አስሬ
የሆነ -ነገርን ኖርኩት እስከ ዛሬ።።

እናም ዛሬ .....
እኔም ልሳሳት ነው ቃላት ልሰርዝ ነው
ምን ልፈጥር ብዬ ብዕሬን ልጥል ነው
ለምን ? ....
ከብዙ ፊደሎች ከብዙ ቃላት ሰልፍ
ደቂቃው ዓመት ነው በጆችሽ ስታቀፍ
ዘለዓለም መሆን ነው ባንቺ ሰማይ ማለፍ
እናም ብቅ ብለሽ
ሳሚኝ በከንፍርሽ።



## ለእናንተ

ምን ነካው ሼክስፒር
እኛ ማለት እኮ ? ..
ሰዎች አይደለንም ሌሎች ፍጥረታት ነን
መነሻው ላይ ቆመን ፍፃሜው የገባን
ድራማውን አውቀን መድረኩን የናቅን
.....
ተቺ ነን ናቂዎች በትንሽ የምንሞት
ሳቁን ውሸት ምንል ያማልክቱን ድርሰት
ሀዘን የሚሰጠን የዘልዓለም እውነት
ስማችን የምንጽፍ በልቦና ሀውልት
ምን ነካው ሼክስፒር
እኛ ማለት እኮ?
.............
ብልጭታ አይደለንም የምድር ተዋናይ
መድረክ ምድር የለንም ጥያቄ እንጂ ሰማይ
ይልቅ
የመድረክ ገንቢ ነን የተውኔት ገምጋሚ
ከምድር ከፍ ብለን ከመካከል ቋሚ
በሞት የሚፈፀም የሕይወት አራሚ
አርመን ላይ ቀና
ታዝበን ላይፀና
መድረክ መፍረስ ላይቀር
ፍጥረት የድርሻውን መራኑን ላይሸር
ፍፃሜ ላይ ጅምር
አዲስ ሌላ ጅምር፤ሃሳብ የንጨምር
እንደዚያ ነን እኛ
ከውሃ ስር ያፈር መድረክ ተገንብቶ
ከውሃ ስር ሌላ እቶን ሃሳብ ፈልቶ
ጥበበኛው እግዜር ...እሳት ስር የነፋስ ማራገቢያ ሰርቶ

ደግሞም በሌላ ቀን
ዶክተሩ ሲጠየቅ በዚህ መስኮት በኩል
እንዴት ቃል አጣፍጦ ህዝብን እንዲደልል
Pain killer ብሎ ውሃ የሚያቀብል
ወለም ያለውን ሰው ላብራቶሪ የሚል፡፡
በዚያም በኩል ቢሆን…
የያንዳንዱን ሰው ቤት አንጀት ያቆሰለ
መፃፍ የሚገባው ስንት በደል አለ፡፡

ተቀማጭ ገጣሚ
ልብ አላለም እንጂ
ያገሪቷ ደም-ስር
ታላቁ ፍርድ ቤት መላ-ቅጥ እንዳጣ
ልብማ ቢል ኖሮ…
እንኳንስ በሌሊት
ምርጥ ሃሳብ ፍለጋ እንቅልፉን ሲያጣ
ጠዋት በማለዳ…
ቡናም ለመጠጣት ከቤቱም ባልወጣ፡፡
ምክንያቱም…
በተወዳጅ ሀገር ድህነት ባጠቃት
ፍትህ ሲጠፋባት
ፍርድ ሲጎልባት
ዋስትናው ምንድን ነው ሰው ወቶ ለመግባት፡፡
ምክንያቱም
በተወዳጅ ሀገር ምርጥ ልጆች ባሏት
የሀይማኖት መሪ…
ከህግ አልባዎች ጋር ህብረት ከፈጠረ
የመስጊድ አገልጋይ…
ከሃሰት ዳኞች ጋር አብሮ ከዘመረ
ድምፁን ጮክ አድርጎ
ታላቁን መጽሃፍ ለህዝብ የሚሰብከው
ቅዱሱን የህይወት አምድ
ክቡሩን የህይወት አፀድ
በፍቃዱ ሲንድ
ክብሩን ጋብቻ ባልጎ ከበከለ



ታዲያ በዚች አገር ምን ቀሪ ተስፋ አለ
ከዚህም የሚልቅ ምንስ ሃሳብ አለ
ሳይፃፍ የሚተው
ዝም ብሎ የሚያልፈው፡፡

…ተቀማጭ ገጣሚ
አላወቀም እንጂ
አውቆማ ቢፅፈው የእውነት ጎዳና
ይገባው ነበረ
በፍርድ ቤት ምክንያት … በፍርድ ቤት ጫና
ፍፁም እንደ ጠፉ
የታላላቅ ሰዎች የእግራቸው ዳና፡፡

ተቀማጭ ገጣሚ
ሃሳብ እያሰበ ብዙ ሃሳብ አለፈው
ሳይፅፍ ሊነጋ ነው፡፡
ተነሳ…
ብትንትን ቢሞቹን በመዳፉ ነጨ
ሲጋራ ባይወድም ሲጋራ አሰኘው
ሰዓቱን ልብ አለ
ውድቅት …
ያውም ዘጠኝ ሰዓት
እንቅልፍን ቻል ብሎ÷ እንቅልፍም ቻል ብሎት፡፡
ያኔ …
የነጋበት ዕለት
ወደኔ ደወለ… ጠዋት ሶስት ሰዓት
ቀን ላይ አገኘሁት
ጨዋታ ጀመረኝ
'ትላንት ማታ'… አለኝ
ጥራት በሌላቸው ዓይኖቹ እያየኝ
የሚገርም ግጥም
ለመሆን የሚችል አንድ ሃሳብ መጥቶልኝ
መፃፍ ግን አቃተኝ፡፡
(አለኝ)
መልሼ ጠየኩት

ዘፋኟ ሃሳብ ናት። የአዲስ ዘመን እዳ
ሃገር ስትሰክር
ጅንስ ሱሪ ቆርጣ… ጅንስ ሱሪ ቀዳ
በመንፈስ በልቧ አውሮፓ ተወልዳ
አገር በሚል ዘፈን እስክታ ምትነዳ
አላወቀም እንጂ
ዳንስ ዎል እስክታዋን
ዘፋኟ እንዳበቃች
የታረሰ መሬት መሣይ ግንባር ይዞ
አፉን ብቻ ይዞ
አካሉ ደንዝዞ
ከባለቤቱ ጋር አርሶ አደር ብቅ አለ
ህይወት ማንነቱን በገፅ እናዳዘለ።
በሳር ቤት ውስጥ ነበረ÷ በፊት የምንኖረው
እግዚአብሔሄር ይመስገን አሁን ቆርቆሮ ነው።
…
ሽንብራ ነበረ በፊት የምንበላው
አልሃም ዱልላሂ አሁን ባቂላ ነው።
…
ተቀማጭ ገጣሚ
አላወቀም እንጂ.. ይህ ነበር የሚፃፍ
ዘመን በመዋጀት ዘመናትን የሚያልፍ
ያውም…
ወረቀት ላይ ሳይሆን ሰማይ ልቦና ላይ
ከሰው ልጆች አልፎ በፈጣሪ እንዲታይ።
…

ተቀጭ ገጣሚ
ዓይኖቹን አልሞ ወረቀቱን አየ
ርዕሱ አለ
በስተ ግራ በኩል ወረቀት አናት ላይ እንደ ተሰቀለ።
አየር ላይ እሮጠ
ያለ ፅንስ አማጠ
ቅዕበታት እሮጡ
ሃሳቦች ሳይመጡ..

አይኖቹን መልሶ ቴሌቭዥንን አየ
ጥቁር ሱፍ አጥልቆ ዜና አንባቢ ታየ።
ፍርድ ቤቱ ብሎ እውነት ተናገረ
ተቀማጭ ገጣሚ
ይህ ሃሳብ እንደሆን ፍፁም አልገባውም
ፍርድ ቤት ነው እንጂ ፍትህ ቤት የለንም
ቢፈርድብን እንጂ ፈርዶልን አያውቅም።
እንደውም
የገዛ ጓደኛው
ታላቅ መፅሃፉ የዘመናት ላቡ በሌቦች ሲሰረቅ
በአይኖቹ አስተውሏል
ማስረጃ እና እውነት ከገንዘብ እንዳይልቅ።

ተቀማጭ ገጣሚ
አላወቀም እንጂ
ልክ በዚህ ሰዓት በአዋጅ ተነግሮ በልቦናው አዝኗል
ሕፃን የደፈረ
ታላቅ ባለስልጣን በዚህ መስኮት ታይቷል
ከሳምንት ኋላ ግን…
ገንዘቡ ፈርዶለት
ህጉ ቸል ብሎት …
ስብሰባ ተቀምጦ ስለ ሴቶች ክብር ሲያወራ ተደምጧል
ደግሞም በሌላ ቀን
ጊዜው ያለፈበት መድሃኒት የሸጠ
ሃገሩን የናቀ በህዝብ ያላገጠ
ያልተፈረደበት
የተፈረደለት
ችግር የለም ብሎ
ነፃ የለቀቀው ታላቁ ፍርድ ቤት ።
ግፈኛ ነጋዴ
ስጋው የገዘፈ መንፈሱ ሚል ዳዴ
የአድዋ እለት…
አይኑን በጨው ታጥቦት…
ስለ ሃገር ፍቅር
ጮክ ብሎ እያወራ ታይቷል በዚህ መስኮት።

ተመሳሳይ ሆኖ ከሚያልፍ ቀን ይልቅ
ሳይሻል አይቀርም በራስ ዓለም መምጠቅ::
*
የራሱ ዓለም-ሰው
ፀሃይን ያያታል
ፀሃይን እያየ
እንዲህ ይለምናል÷ እንዲህ ይማፀናል
ለ'ኔ ግን ባልወጣሽ÷ በቀረሽ ይላታል
የራሱ ዓለም ሰው...
ጨረቃን ያያታል..
ጨረቃን እያየ እንዲህ ይለምናል
እንዲህ ይማፀናል
እንደ ሰዋ ሕይወት
ሙሉና ጎዶሎ ዋጋ ቢስ ይላታል
የራሱ ዓለም ሰው
ሰማዩን ያየዋል
ውሃ ይመስለዋል ሰሪው ይጠሩዋል
* * *
የራሱ ዓለም ሰው
ሁሉን ነገር ያያል
ሁሉም ያስጠላዋል...
ለራሱ ዓለም ሰው ...
በፈጠረው ዓለም÷ የራስ ዓለም ዓለው
በፍቅሩዋ ሲሰቃይ ደስታ የምትሰጠው
እምሀ ሠጥቷታል
ብዙ ደምቶላታል
ወርቅ እጣን ያይደለ÷ እንባን ለግሷታል
አምላኩ እሷው ነች
ክንዶቹን ታቅፋ ሌሊቱን ያነጋች
የራሱ ዓለም ሰው
የራስ አምላክ አለው ለፈጠረው ዓለም
አምላኩ ምንም ነው:: ምንም ነገር ምንም
ራሡ ፍቅርም

*ለፋሲል ረታ + ለሕዝቅኤል ሠብስቤ Oldies እና አማር ሃያም ለነበሩን ጊዚያቶች

## ሃሳብ

እግዜር ጨካኝ ቢሆን
ባያዝንለት ኖሮ ..ሰው ለሚባል ፍጡር
በፍለጋ እንዲያብድ
ፈጣሪህ ነኝ ብሎ አይነግረውም ነበር፡፡...

## ያፈር ዕንባ ጊሜ

አምና…

ደመናዎች ቀሩ
ሠይጣናት ዘመሩ
ክፉዎች አበሩ፡፡…
ውቅያኖስ አነባ፡.. ሸሸ ከሌላ አምባ፡፡
ዘንድሮ

ሠማያት ጠቆሩ
ደመናዎች ዞሩ
ገበሬዎች ዘሩ
ደረሠ መኸሩ፡፡
*

ቢሆንም

አጫጆች መላእክት
መላእክትም ማለት?…
፩
ቆራጮች ነገሥታት
፪
ፈላጮች መኳንንት
፫
አድር ባይ ሹማምንት

እነዚህ ተባብረው
ባንድ ተሠልፈው
'ሠይፍ' ይዘው ቢያይዋት
አለቀሰች ምድር ያፈር ዕንባ 'ጊሜ'
ባ'ዳም ሠበብ ቢሞት ያ'ዳም ዘር አዳሜ፡፡

## የራሱ ዓለም ሰው

የራሱ ዓለም ሰው…
ከናት.. ከአባቱ
ከወንድም.. ከእህቱ… አብሮ ተቀምጧል
አብረውት አይደሉም፡፡
አባቱን አይሰማም
እናቱን አያይም
ለብቻው ይጓዛል በፈጠረው ዓለም፡፡
* * *

በራስ አለም መሃል
አይደለም ከሰዎች…
አይጠፉም አንዳንዴ ከራስም መነጠል
*

የራሱ ዓለም ሰው
የእኔ ከሚላቸው ÷ አብሮ አደጎቹ
ውሃ ከረጫቸው ከ'ኩል ጓደኞቹ
ጭቃ ካቧካቸው ከሰፈር ልጆቹ
አብሮ ተቀምጧል…
አብሯቸው አይደለም
ለብቻው ነው ጉዞው በፈጠረው ዓለም

በይሉኝታ ምክንያት
አብሮ ከመዳመር÷ ከንቶ ፈንቶ ኑሮ
ሳይሻል አይቀርም የብቻ እንጉርጉሮ፡፡
* * *

የራሱ ዓለም ሰው
ካንድ ክፍል ቤቱ ዘግቶ ተቀምጧል
የሚያነበው መፅሀፍ ከመሬት ላይ ወድቋል
ሩኹን ስቶታል፡፡
ጠዋት እንደ ላከ
ዐይኑን ወደ ጣሪያ ወዴትም ሃሳቡን
እንዴት እንደው ሳያውቅ አገባዷል ቀኑን፡፡
* * *

ዛሬም እንደትናንት



Scanned by CamScanner

እንቅልፍ የናፈቀ አይኑን እያየሁት
'ርዕሱ ምንድን ነው'
ወይም
ሃሳቡ ምንድን ነው'
ድምፁን ዝቅ አድርጎ
ከጎናችን ያሉት-ቡና የሚጠጡት
ድምፁን እንዳይሰሙት
ሃሳብ እናዳይሰርቁት
በጆሮዬ በኩል
ያልፃፈውን ሃሳብ
ርዕሱን ተናግረው
ርዕሱ
"እንደዚህማ ከሆነ ሃገሬ የምትጓዘው
እንደዚህማ ከሆነ ሃገሬ ምትቀጥለው
አማራጩ ጦርነት ነው።"
የሚል ነው፡

.....

ታዲያ እኔ
ከዚያን ቀን በኋላ አንዳንዴ ሳስበው
እስከ ዛሬ ድረስ
ለጆሮ መታመም የተዳረኩትኝ.. በዚህ..ምክንያት ነው።

Scanned by CamScanner

## ዜሮ+ዜሮ

ምንም ከነበረው
ደርቆ ከምናየው÷ ከባዶ ላይ ቅዳ
ይህ ነው የህይወት ትርጉም÷የመፈጠር እዳ
ምንጬም ባዶ ባይሆን- መቅጃው ነው ቀዳዳ፡፡
ፍፁም እናዳታስብ
ስለ እንስራው ክፍተት
ባዶን ስለ-መቅዳት
አይሞላም-ሽንቁር ነው የህይወት እንስራ
በፈገግታህ በኩል ይመጣል መከራ!!
ነገር ግን ተጠንቀቅ...
ውሃ ልትቀዳ- ከምንጩ ስትጠልቅ
አሸዋውን- ዝቀህ እንስራው እንዳይደቅ፡፡

## መሃል

መጽሐፉን ገለጠ...
ግሳጩ መጽሐፍ የሆነ ቦታ ላይ
የደራሲው ሀሳብ እዲህ ይነበባል
መጽሐፉን የያዘው የደራሲው ወዳጅ...
ገባኝ የሚለው ቃል ያልገባው ይመስላል፡፡

መጽሐፉ
መሃል ይታሰባል
መሃል ያሳስባል
ቀለም አይበቃወም ከቃላት ከፍ ይላል
የህጻናት እንቅልፍ ጣፋጭ ህልም ይመስላል
ይላል...
ደግሞም መልካም ህልም የረሱት
እጅግ ጥልቅ እንቅልፍ ለአጭር ሰዓት የተኙት
ይላል
ስለዚህ - መሃል አይወራም
ህልም እንኳ ትዝ ብሎ... ቢወራ ቢዘከር
አጭር ጣፋጭ እንቅልፍ እንዲህ ነው ተብሎ
አይችልም ሲነገር፡፡

ውበት አስታወሠ
በሃሳብ መጽሐፍ ህልሞቹን ዳሰሰ
የሳሮን የጀዝሚን የአበቦች ጉዝጓዝ
የልጅቷ ፀጉር...
ጨረቃ መደብ ላይ የሚፈስ ጥቁር ወንዝ
ይመስላል፡፡...
አይኖቹ እረፍት አጡ
ድብቅ ውበቶቿ በዝተው ገሃድ ወጡ
የሚያፈቅራትን ሴት ነፍሷን አስተዋለ
ሠማይ መጠን ፍቅር
ወደ ውጭ የሚረጭ ዓይኗ ስር ዓይን አለ፡፡
አየ ተገረመ
ከናፍሯን ሳመ



Scanned by CamScanner

ውበት የማይገባት
ናፍቆት የማይሰማት
ቁመኛን አፍቅሬ ነፍሴን ከሚጨንቃት
ለምን ዝም አልልም።
ምክንያቱም
ምክንያቱም ታውቂያለሽ...
የወንድ ልጅ - ሕይወት?
የወንድ ልጅ- ሕይወት!!!
አንድም ካገሩ ሚፍ ከጠላቶቹ ቀስት
አንድም ከፍቅረኛው ከሴት መዳፍ ላይ ናት
ይኸው
ይኸው ደስ ይበልሽ
መዳፈን አንስቼ ከንፈሬ ላይ ጫንኩኝ
ዝምታ አሸለበኝ እንቅልፍ አስፈራራኝ
ይኸው ደስ ይበልሽ ?
እኔ አንቺን መረጥኩኝ
እኔ አንቺን ወደድኩኝ
እኔ በንቺ ሞትኩኝ!!!------------

## ምናባዊ ጽንፎች

ክንፍ አብቅዬ ነበር...
እንዳንደኛው መላክ ከሰማይ እንዳለው
መንኩራኩር ሆኜ ሕዋውን ልቀዝፈው
ይኸውልሽ ውዴ...
አመፀኛው ልቤ ክንፉን ያበቀለው
ሊንሳፈፍ አይደለም..
ወደ ሰማይ ውቶ ምስጋናን እንዲሰጠው
አይደለም...
አይደለም
ክንፉን ያበቀለው..
ላንቺ ያለኝ ፍቅር ነው...
ላንቺ ያለኝ መውደድ ነው
...
ይኸውልሽ ፍቅሬ
ይኼ ክፉ ልቤ ክንፉን ያበቀለው
ትላንትና ማታ ከኔ ሥትለዪ.. ፊትሽን ሥላጣው
በሌሊት በረሬ..
ከደጃሽ ወድቄ እንዴት ነሽ ልልሽ ነው።

Scanned by CamScanner

# ቡና ጣዕም ናፍቆት

የተነነ ውሃ ርጥብ የሕይወት አልማዝ
ገላዬን አራሰው
ፀጉሬን አጨቀየው
ዝናብ በሚተፋ በሌሊት ቁር መሃል
አንቺን እያሰብኩኝ..
ነፍሴን አዝላለሁ
ዓይኔን አረጥባለሁ...
ይኸው....
ዓይኔ ሥቁረት መሃል...
ናፍቆት የጠመቀው የእንባ ወይን ወደቀ
ረዥም መንገድ ላይ..
ለብቻ እየተንዝኩ በደረቀ- አፈር.. አውራ.. ጣቴ- አለቀ::
ስምሽን ጠራሁት...
ስምሽን ስጠራ ያቀፍኩሽ መሰለኝ
በስምሽ አቅፌ ደሜን ጠረኩትኝ
ለምን እንደሁ እንጃ?...
እስከ ዛሬ ድረስ...
የምወደው ቡና- ላይ- ምጨምረው ስኳር
የአጭር ፍቅራችንን አጭር ትዝታ ነው::
እንዴት ይጣፍጣል
ኪዳነ-ምህረትን... እንደውም ሲመስለኝ
የኖርኩረት ለዚህ ነው
አልያም ስለዚህ ነው::
(እንዴት እንደሁ እንጃ...
በሃጢአት ስሰክር.. ሰክሬ ስጸጸት...
በሚፈስ እንባዬ ማልመው አንቺን ነው
ድንገት...
ቡና ስኒ እድሜ- ቡና ጣዕም ናፍቆት- መንፈሴን ሰበረው
ታዲያ...
በበደል ተነክሮ ንጹህ ፍቅርን ማሸተት ምን ይሉት ፈሊጥ ነው...
እያልኩኝ ባስብም...
በዚህ መሀል እንኳ ማስበው አንቺን ነው...
ለምን እንደሁ እንጃ...



Scanned by CamScanner

## ለሊት መሰል ዝምታ

እንዳንቺ ቅላጼ…ወፎች ላይችሉበት
ነፋሣት ላይፈጥሩት
ፅናፅሉን ይዘው ቄሶች ላያዜሙት
እሰማው ይመስል ድምፅሽን ፈለግሁት
ፈለግኩት ፍቅሬ ሆይ…
ቅንፍ ቅንድብሽ ሥር
ዓይንሽ መስሎኝ ባሕር
እንደ መርከብ ጭኖ ይሉኝታን የሚያበር
ልገባ ብሻ ከውስጡ
ልዋኝ ብጠጋ ከስምጡ
ፀጉርሽ መሐል እንድታሰር
በልቦናሽ እንድፈቀር
በክናድሽ ለመታቀፍ
ከከንፈርሽ የማር ሰፈፍ
ለመቅሰም ፈልጌ..
ለሊት መሰል ዝምታሽን እርሱን ግን ፈራሁት
ግና ብፈራውም አለሁ በደጅ ፅናት
ዛሬም ደግሞ እናዳለፈው ትላንት
ከዝምታሽ በላይ
ያ'ራዊቶች ጩኸት የኔ ልብ አይፈራም
ታላቅ የመብረቅ ድምፅ እኔን አያስጋም
ውበትሽ ላይ ዝምታሽ ነው ደጅ ጠኚ ያደረገኝ
ደፋር ልቤ ያስፈራራኝ
ዝምታሽ ዝም እስኪል…
ዓይኖችሽ ልቤ ውስጥ መጥተው እስኪጠልቁ
ዐይኔና ጥርሶችሽ እስኪተዋወቁ
ያለፈን ረስተው ዛሬን እስኪያጸድቁ
እጠብቅሻለሁ ሁሌም በደጅ ጥናት
ዛሬም ደግሞ እንዳለፈው ትላንት
እንዳንቺማ…
በቅጠሎች መሀል ነፋሳት አይፈጥሩት
ፅናፅሉን ይዘው ቄሶች አያዜሙት
ከዐለት ተጋጭተው ወንዞች አይችሉበት



ውዴ ምነው…
ባየሽልኝ ከዋክብቱን
ካ'ይንሽ ወስደው ብርሃናቱን
እቴ ምነው…
ባሸተትሽው ናርዶሱን
ናርዶሱ ሲል አንቺን አንቺን
ምነው ፍቅሬ በሰማሽው የወፎቹን
ወፍ ወፍ የሚል ወፍ ዝማሬን
ካንቺ ነስተው ቅላፄውን…
እንዳንቺማ….
እንኳን ነፋሳቱ…..
እንኳን ቀላያቱ….
እንኳን አእዋፉ እንኳን ቀሳውስቱ
እንጃ መላዕክቱ ከሰማይ ያሉቱ
አንቺን የማውቅ እኔ….
በልቦናሽ እስክፈቀር
ፀጉርሽ መሀል እስክታሰር
በክናድሽ እስክታቀፍ
ዝምታሽ ዝም እስኪል መዝሙር እስኪሰማ
እጠብቅሻለሁ ሁሌም በደጅ ጥናት
ዛሬም ደግሞ
……እንዳለፈው ትላንት



Scanned by CamScanner

(ካንገቱ ዝቅ አለ)

ቆመው ሚደንሱ ጡቶቿ መካከል
ልጅነት እድሜዋ ሽቶና ውበቷ ሶስቱ ተጽፈዋል
ጆሮዋ ስር ገብቶ በልስልስ ሹክሹክታ..
ይሄ ሁሉ ውበት ግዛቴ ነው አለ
ዓይኑን ባይኗ እያየች ፍቅር እየማለች
ይሄ ሁሉ ውበት ያንድ አንተ ነው አለች
(ካንገቱ ዝቅ አለ)

አንገቷን ተሳልሞ
በሰስ ጡቶቿ ጫፍ በልስልስ ምላሱ እንጆሪ ቆርጥሞ
ወደታች ዝቅ ሲል...
ከእምብርቷ ምንጭ ስር ሆዷ ላይ ፈገግታ
በደማቅ ተጽፏል
ፍቅር ጠልቆ ጠጣ
ስጋው ከነፍስ ወጣ
ያሉበትን ስፍራ ቤቱን አስተዋለው
ሰማያዊ ጣራ ፍቅር  የተጠለፈ
አረንጓዴ ወለል ሰላም የሚል ፊደል ውስጡ የተጻፈ
በሩ ሰፊ ቅጠል አረፍት የዘፈነ
የታጋሽ ልቦና...
እጅግ ትልቅ መስኮት በሃምራዊ ሃረግ የተሸፋፈነ
(መሆኑን ልብ አለ)

ከናፍሯን ሳመ ውበቷን ደገመ
ዘወትር አዲስ መስሎ ቀልቡን ከሚነሳው
ውብ የመሃል ውበት ሃሳቡን ከተተው

(ካሳቡ ባነነ)
ሌላ ገፅ ገለጠ
ግላጩ መፅሐፍ አልባቱ መሃል ምልክት ለማኖር ብዕር አስቀመጠ
አይኖቹን ጨፍኖ ያነበበውን ቃል ሊያስብ ተመሰጠ።
ውብ ቅኔ ነው አለ
ግራው ቀኙ ዳሩ መንፈስ የውሃ ጣዕም

አጭር ጣፋጭ እንቅልፍ
ልብ ልቦና ላይ ይታሰባል እንጂ እንደመልካም ግጥም
መሃል አይወራም መሃል ይታሰባል
ቀለም አይበቃውም ከቃላት ከፍ ይላል

ምናልባት ደራሲ
አፈንጋጭ ነኝ ብሎ ህይወት ከነብጉር ማሳየት ነው ብሎ
መሃልን ቢጽፈው
የመሃል ውበቱ ብጉር ነው ሚሆነው
ምናልባት ሰዓሊ
አፈንጋጭ ነኝ ብሎ የመሃልን ውበት ስየዋለሁ ቢልህ
አጭር ጣፋጭ እንቅልፍ
ይህንን ይመስላል ብሎ ነው ሚዋሽህ
አጭር ጣፋጭ እንቅልፍ
በምን ቃል ይወራል
አጭር ጣፋጭ እንቅልፍ እንዲህ ነው እንዳይባል
ከቀለማት አቅም  ከቃላት ከፍ ይላል።
.

መሃል አይወራም መሃል ይታሰባል
መሃል አይወራም መሀል ያሳስባል
የሚሉትን ቃላት አስቦ ሲጨርስ ይህን ቃል ደገመው
መሃል ትዝታ ነው
ያድራሽ የተመላሽ የረፍት ስፍራ ነው
መሃል ቀለም አልባ መሃል ቃል አልባ ነው
ዝም የሚሉት ቅኝት የራስ ዝማሬ ነው
እናም በዚህ ምክንያት ነው...
ዜማና ሙዚቃ ግጥምና ስዕል ተስርቶ ማያልቀው
መሃል ቃል የለውም...
ቃል ቢኖረው እንኳ መናፈቅ ብቻ ነው
እንጂ....
እያንዳንዱ ጠቢብ የመሀልን ውበት
ተጠቦ ቢያገኘው
ለዚህ ታላቅ ውበት
አንድ መልካም ቅኔ አንድ ሙዚቃና አንድ ስዕል በቂ ነው



Scanned by CamScanner

ከግጥም
ከስዕል
ከሙዚቃው በላይ
እርሷን ስለሆነ አስበልጬ የማይ
እባክህ ሠማይ ሆይ።???"



## በሌላኛው በኩል

*

ሰው ሆይ
መንገድህን መንገድ ስጠው..
በሌላኛው መንገድ በኩል
መንገደኛው በጠቅላላ.. በዚህ በኩል ሁሉም ያልፋል።
*

አንድ መንገድ የሠነፍ ነው
ብቸኝነት የሚፈራ መንጋ ሚሆን በጠቅላላ
ከማታየው ወዲያ ማዶ..
ከምታየው ወደኋላ...
የብቸኞች ቀጭን መንገድ...
የብቸኞች ምርጥ ሃሳብ ነው ይህቺን ዓለም የሚያበላ
ይቺን አለም የሚበላ..
ስለዚህ ገለል በል....
*

ከመንገኞች ጉዞ መሃል
ብቸኛው ሰው ገጭቶህ ያልፋል
አሊያም ሸልኮ ይቀድምሃል
ጥንትስ ቢሆን
ምርጥ ታሪክ በብዙዎች መች ተሰርቷል...?
ብቸኛው ሰው ይቀድምሃል
በሌላኛው መንገድ በኩል
*

አብሮ ተጓዥ መንገደኛ
ባንተ ማለፍ ይሳሳቃል
ባንተ ማለፍ ይሳቀቃል
ምክንያቱም....
ከተሰራው መንገድ በቀር ያንተን መንገድ መች ያውቀዋል
ይኸው....
በቅጠሉ በአበባው በቀጭን ሳር ልቦና ላይ
ብሌን መጠን ውሃ ቆሟል...
ጤዛው ያልፋል....
እምባ መጠን ያ ጠብታ
ለሳሩና.. ለቅጠሉ ደራሽ ውሃ ወንዝ ይሆናል

Scanned by CamScanner

እንኳን ለህዝብ ዓይን.. ለራሷ የሚጎድል
ስዕል ትስላለለች
እኔን.. በሁለት ዓይኗ አትኩራ እያየች፡፡
እንደዛ ስታየኝ...
ስለእርሷ አስባለሁ
ስለእርሷ እሰጋለሁ
የፍርሃቴን አዝማች ደግሜ አዜማለሁ
ጥበብ ማፍቀር መልካም
ጥበብ መውደድ መልካም
ግን
በማፍቀር ምክንያት ለመሆን መታገል
እጅግ ታላቅ በደል...
-
ደግሞ ሌላ ጊዜ
ሀሳብ መጣ ብላ
እኔን ወዲያ ጥላ...
ከሞቀ አልጋዋ ተስፈንጥራ ወርዳ
ዕሁፍ ትፅፋለች በድሪቶ ቃላት ከወረቀት ሜዳ
እናም...
ድሪቶውን ቃላት በቀለም አጥብባ
ሃሳብ ነው ትላለች ተጨንቃ ተጠባ
ያውም ፖለቲካ
የሀገሪትዋን ሰዎች ልቦና ሚነካ...
ልክ...
ከፓስታው ላይ ስጎ ከስጎ ላይ እርጎ
ከእርጎ በላይም.. ሙዝ... ከሙዙ ላይ ሽሮ...
ቅጡ ያልተለየ .. ጉልባን የሚመስል... ከሽሮ ላይ ጎፍሮ...
ከጎፍሮ ጫፍ አጥንት ተግጦ ያለቀ
የቀን ቤት ለመምታት
አላለቀም ብለው ግማሽ የሚያነቡት



የእኛን ሀገር አይነት የሚመስል ሕይወት
አይነት ግጥም...
ያውም ፖለቲካ...
ያገሪቷን ሰዎች ልቦና ሚነካ
...
እኔ...
በዚህ ሁሉ መሃል
መውደዷን እያየሁ.. ማፍቀሯን እያየሁ
መልካም ነው እላለሁ
ደግሞም...
መውደዷን እያየሁ
ማፍቀሯን እያየሁ...እንዲህ እሰጋለሁ
"ያለመሆን እውነት
የመሆን መሻቷን... ከንቱ ምኞት የነጠቃት ለታ
እንዳገኝ አውቃለሁ...
እርሷ ሳሉን መሃል ፍቅር እራሷ ሞታ
ጥበብ ስፍራ አጥታ"
...
እናም ይህ እንዳይሆን...
ሁሉን ለሚሰጠው
አልቦ ለሚሳነው
እንዲ'እጸልያለሁ
እንዲ እማጸናለሁ...
"እባክህ ጌታ ሆይ.....
የእርሷን ታላቅ ፍቅር ጥበብ አምልኮዋን ለእኔ አድርገውና
የእኔን- ደግሞ መከሊት...ታላቅ ስጦታህን...ለእርሷ ሸልም
ውሰድና፡፡...
ምክንያቱም...
ከፍቅር የሚልቅ ምንም የለምና
ደግሞም... ለእኔ ከሰጠኸው

## የሁለት ዘለዓለሞች ስጦታ

ባልነበርኩበት ወቅት
ባልታየሁበት ቀን
ከኔ በፊት ባለች የዘላ'ለም ዕድሜ
በማልኖራት ጊዜ
ሳላያት በምትኖር የሞት ኋላ ህልሜ
በማልኖራት ሕይወት
ብኖር በምጓጓት
ላላየኋት ዕለት
ትዝታ ለሌላት
በሁለት ዘላ'ለሞች ፍቅርሽን አሰርኩት።

ምክንያቱም...
አሁን የምሳሳት የምኖራት ሕይወት
ዋጋ ስለማትሆን እውነት ለሰጠች ሴት
ነፋስ ስለሆነች ምሳሌና ተረት
ተረት 'ኔ እንድሆን ዛሬን ለእኔ ተውኩት።

ይልቅስ እነሆኝ..
ክብር ለተሞላው ለታሰረው ፍቅርሽ
ተቀበይ ስጦታ ተቀበይ ኑዛዜ
እኔን ላሁን ትቼ ላንቺ ሰጥቻለሁ..
ከኔነቴ ኋላ ከኔነቴ በፊት የሚኖርን ጊዜ...።



## መክሊት እና ፍቅር

እርሷ...
ጥበብ ትወዳለች.. ከራስ ፍቅር በላይ
ከውበቷ በላይ።
...
እርሱ
ባይወድም በግዱ የመክሊት ተቀባይ
ከሕይወቱ በላይ።...
...
እርሷ
ስዕል ትስላለች
ግጥም ትፅፋለች
የሙዚቃም ድርሰት ትሞካክራለች
ከመውደዷ ይልቅ መሆን ትመኛለች።...
እርሱ ...
በፀጥታው ምሽት እርሷን ልብ እያለ
የትግል ጥበቧን እንደዚህ ነው አለ
ጥበብ ማፍቀር መልካም
ጥበብ መውደድ መልካም
ግን...
በመውደድ ምክንያት... ለመሆን መዳከም
እጅግ ታላቅ ህመም።...
እያለ ይሰጋል...
ስለ'ርሷ ያስባል።...
...
እርሷ.. ባሰኛት ቀን
ስዕል ትስላለች
የዶሮ ጭረቶች የማይረባ ምስል
የእኔን የባሏን ጭቅጭቅ ሚመስል



Scanned by CamScanner

# አባይ ፪

አሁን ደግሞ ተኛ..
ጥቂት ዐረፍ በል
ጥቂት ጋደም በል..
አንተ ክቡር ውሃ ለብዙ ዘመናት ስትጓዝ ኖረሃል
የተኛህበትን አፈርህን ጠርገህ
ግንድ ግራር ነቅለህ
ካልተሰራሕበት
ካልመነጨኽበት...
ካልተተከልክበት...
ረፍት ያለ መስሎህ ብዙ ተሰደሀል
ለረፍት አልባ ጊዜያት
ለዕልፍ ዘመናት...
ያገርህን ሰዎች በግብር መስለሃል
አልያም ምሣሌውን ካንተ ተምረዋል
ምክንያቱም....
የወንዝም የሕዝብም ህልምና ተስፋቸው ከሰው ሃገር ወድቋል ...
አሁን ግና ተኛ
ጥቂት ጋደም በል
ጥቂት አረፍ በል
ለብዙዎች እረፍት..
ከመነጨሕበት መሬት ላይ ተንጋለል
“ለምን?”... ብትል...
በተፈጥሮም ትዕዛዝ...
አንዳንዴ ለማለም መተኛት ግድ ይላል
ውብ አበቦች ፍጠር...
አረንጓዴ ቅጠል የተስፋ ሐገር አልም::
አባይ መተረቻ
አባይ ተረት ብቻ
የተራ ዘፋኞች የቃል መጫወቻ
(ሆነህ ቆይተሃል)
እስከመቼ ድረስ
በወንዝ የሚዘረፍ የቃላት ጨዋታ ይሄ ሕዝብ ይችላል?
እባክህን አባይ...

ጥቂት ጋደም በል
ትንሽ አረፍ በል
እንደ እባብ በልብኽ.....
ተስቦ መሠደድ ተሰዶ መደፍረስ
ያለ ቦታህ ማጌጥ ያላገርህ መንገሥ
የራስ ልጅ ሲያነባ የጎረቤት ማበስ
ባልሆኑት መወደስ ባልገነቡት መግነን
ዘፈን
የውሸት ዘፈን አባይ ግዮን መባል
(ባክህ ይበቃሃል)
አባይ ያገር ሢሣይ
አባይ የህዝብ ፀሀይ ብትሆን ይሻልሃል።
አባይ ይበቃሃል
አሁን አረፍ በል
በጀርባህ ተንጋለል...
የዚህን ምስኪን ሕዝብ...
ፈገግታና ሳቁን ከፊቱ ላይ ጠርገህ በ'ንባ ተክተሃል
የወንዝነት በደል...
ያለ ሐገር መብቀል..ያለ ሐገር ማብቀል
ከሚመነጩበት ከሞሉበት መጉደል
ሕዝቡ ሥለበቃው...
ግፍህ ሥለገፋው ይበቃል.. ብሎሃል
(ይበቃኛል በለው)...
ይበቃሃል ግዮን
ሳይፈፅሙ መጓዝ ያለ ሕልም መፍሰስ
እዚህ ደም ማስለቀስ እዚያ ዕንባን ማበስ
የራስ ጎጆን ንቆ....
መሠረት በሌለው..ባሸዋ በፀና በሠው ቤት መኮፈስ
(ይበቃኛል በለው)....
ምክንያቱም
ያልደከመ አይወድቅም
ያልወደቀ አይተኛም
ያልተኛ አያልምም...
እናም...
ለማለም ቆም በል በመጠን አሸልብ



Scanned by CamScanner

አቧራውን ገፎ ሚጥል
በሌላኛው መንገድ በኩል
እናም...
ሰው ሆይ...
መንገድህን መንገድ ስጠው
በሌላኛው መንገድ በኩል...
መንገደኛው በጠቅላላ.. በዚህ በኩል.. ማንም ያልፋል

## ከፋቃሪው ፍቅር

ከወንዞች ድንጋይ ላይ ከባህር ዳርቻ
ወይም ከጥቅጥቅ ደን ከዋሻ ስርቻ
ሁለታችን ብቻ
ሽሙጥ ከበዛበት ሃሜተኛ ዓለም
እንስሳት ከፈሩት ካ'ራዊቶች ገዳም
አናብስት ካሉበት ከበረሃዎቹ ሳር
ወይም ከጨለማው ጭፍቅ ካለው ዱር
ይህን የድንጋይ ዱር ከተማውን ንቀን
ሁለታችን ብቻ
ከምንጭ ውሃ ቀድተን
ለምለም ሳር ላይ አርፈን
ከሰው እፎይ ብለን
ካ'ራዊት ተዛምደን
ይህን ዓለም ንቀን
የሁለት ዓለም ፈጥረን
.. መኖር ብንጀምር..
ከወንዞች ድንጋይ ላይ ከባህር ዳርቻ
ወይም ከጥቅጥቅ ደን ከዋሻ ስርቻ
መኖር ብንጀምር..
በፍቅራችን ቀንቶ ፍቅር ይሰደዳል
ፍቅርም በራሱ ፍቅሩን ይፈልጋል
ፍቅሩን ለማግኘትም
በንፋስ ኮሽታ እኛን ያጋጩናል
ምክንያቱም
ፍቅርም ከዱር ወ'ቶ ፍቅሩን ይፈልጋል
ቅናትን ሳይሰማት አንድ ቀን መች ያድራል።

## ምናልባት

ሕፃኑ ልጅ ጮኸ...
ምንም ከዓላዩት ከዕሩይ ዓይኖቹ ዕንባን አስቀደመ
ታላቁ ሠው ሔደ...
ፀጥ ብሎ ተኛ በወላጆቹ 'ንባ ጉዞው ተፈፀመ።

የመጣውን ሕፃን...
በነጭ ፈትል ጨርቅ ገላውን ሸፈነው
ታላቁን ተጓኘ ሰው...
በሕፃኑ ዐይነት...
በነጭ ፈትል ጨርቅ ጠቅልለን ሸኘነው...
ወላጂቱ ትስቃለች
የልጇን ጣት ትቆጥራለች
የተጓኘ ሚስት ታነባለች
ልጆቿ መልክ ላይ ባሏን ታስባለች
መወለድ መፈጠር
መሞት አለመኖር
መፈጠር ለመሞት የሚደረግ ፍጥነት
መሞት መሰናበት...
የልጅነት ዕንባን አስረክቦ መውጣት
ኦ...
ክርስቶስ....
ምን አይነት ሕግ ነው ምን አይነት ስርዓት?
ሲጓዙ ፀጥ ብሎ ሲመጡ ደም ማንባት
ናፍቆት ነው መሰለኝ.... ናፍቆት ነው... ናፍቆት ነው...
ካገሩ የራቀ ካገሩ ሲመለስ
የልጅነት ሚስቱን የትውልድ አገሩን ናፍቆ እንደሚያለቅስ
ሕፃኑም እንዲያ ነው...
መሬቱን ያውቀዋል
ናፍቆ ነው ያነባው ከዚህ ቀደም መጥቷል።
ማን ያውቃል አንድ ቀን የናፈቁት ዕለት
አልቅሰው የሸኙት ሲያለቅስ እንደሚያዩት

## መኻገድ አለመስሎት

•

ቀድሞ በተሰራው በነበረው መጓዝ
ለመፍጠር መዳከም...
በነበረው መፍዘዝ የራስ አለመያዝ...
የሰውን ከተማ.. ልቦናውን ሞላው
የተመልካችን ዓይን መድገም አሰቃየው
•

አዲስ ነገር ፈራን
አዲስ ሲሞከርም ባለመቻል ስጋት የሰራውን ተቸን
እናም...
እናም በዚህ ምክንያት የቁም ሞትን ሞትን!!!...

....
የቁም ሞት ሚልን ቃል
እንተርጉመው ብንል
ሊሳ ምንም አይሆን.. ምንምም አይባል።
የቁም ሞት ትርጉሙ
አዲስ ነገር ብለው.. ነበርን ሲደግሙ።

....
የቁም ሞት ትርጉሙ
የቁም ሞት ትርጉሙ
በጥበብ ማህፀን....
አንድ አይነት መልክ ይዘው... ሙዚቃና... ግጥም... ድርሰትና ስዕል
አባራ ሊቅሙ .. መሬት ላይ ሲወድቁ.. ተወለዱ ሲባል።...
የቁም ሞት ይሆናል።......።......።......



Scanned by CamScanner

ባገርህ መሬት ላይ-ላገር ልጅ ተሠብሠብ
ረፍት አድርግና... ለሕዝብ እረፍት ሁን
ሕዝብሕን ደክሞታል..
ያንተን ተራ ተረት..
አባይ... ትልቁ አባይ ከሚለው ቃል በቀር
ከስም ያላለፈ ተግባር አልባ ቃላት ጀሮው ሠልችቶታል
የግብፅ የቤት ሥራም በወሬህ ተከድኗል
ሥለዚህ ይበቃል።
አባይ መተረቻ
አባይ ተረት ብቻ
የተራ ገጣሚ የቃል መጫወቻ-ሆነህ ቆይተሃል
አሑን ግን ይበቃል...
(ሕልም አለብኝ በለው....
እናም ሕልሜን ላልም እያሸለበኝ ነው በልና ተናገር
የወንዝነት በደል እንደበቃህ መስክር....
ኢትዮጲያ ሠማይ ላይ ዐይኖችህን አትኩር።
ጥልቅ ዕንቅልፍ እሥኪሆን
በጀርባህ ተኝተህ ከዋክብቶች ቁጠር
ምክንያት...
ያልደከመ አይወድቅም
ያልወደቀ አይተኛም
ያልተኛ አያልምም.. ያላለመ አይኖርም...
ሥለዚህ...
ሕልምሕን ለማየት..
አሑን ረፍት አድርግ ጥቂት ጋደም በል
ብዙ ዘመን ያለው።
ትልቅ ረኸርም ወንዝ መባል ይበቃሃል።
አባይ ያገር ሢሣይ
አባይ የህዝብ ፀሃይ ..ብቶን ይሻልሃል ብቶን ይበጅሃል።

## ቢቸግር ጤፍ ብድር

በፊት መጀመሪያው
ሆኖ ለነበረው 'ቃል' ነበረ ስሙ
አስቀድሞ ላለው ከ'ምን' ከ'ምንሙ'!!!
ሰዎች ግን ሰነፉ
ሠንፈውም አጠፉ
'እግዚአብሔር' ብለው
በነርሱ መጠን ልክ አዲስ 'ስምን' ፃፉ።



Scanned by CamScanner

ልብን የሚያስተከዝ ደም ዕንባ ያነባል
ወረቀት ጽናሕ ላይ ፊደል ዕጣን ያጥናል...
ካህሊል ጂብራን ካህሊል።...
የሊባኖስ ልውል።...
.....
ያንን ያስብና ይህንን ይፅፋል...
ትንሽ ደከም ሲል...
ከጠረጴዛው ላይ አንገቱን ይደፋል...
ካንድ ክፍል ቤቱ...
አንገቱን ሲደፋ...
ነፍሱ ካለችበት ካ'ማልከት ወለል
ከመቅደሱ ደጃፍ በጉልበቱ ወድቋል
ከዚህ ሁሉ ኋላ...
እውነተኛ ዕንባውን በእጆቹ ዳብሶ
የነፍሱን ማረፊያ ከሥጋው መልሶ
ትንሽ እንዳሰበ....
በሃያ ዓመት ዕድሜው
ያረፈች እናቱን 'ካሚላን' ያስባል
ያዝናል
ይተከዛል
አሁንም ዳግመኛ
ትካዜን ለማጥፋት ሀዘንን ለመርሳት
አራት መሥመር ግጥም.... ማንበብ ይጀምራል
ግጥሙ...
"ጥበብን ከሴቶች
ወይንን ከውበት እጅ ለመቅዳት ተወለድኩ
እንኳን ካንቺ ሥጋ ውብ ሥጋሽን ወሰድኩ
እንኳንም ካንቺ ደም ጥበብ ደምን ቀዳሁ
ያኔ በናትነት...
ንፍገት በሌለው እጅ ያሥተማርሽኝ ፍቅር
ይኸው ክንፍ ሆነልኝ...
በብሩሽ በእርሳስ ዓለምን የሚዞር"
ካህሊል ጂብራን ካህሊል
የሊባኖስ ልውል።

## የማርያም ንግሥ ዕለት

የማርያም ንግሥ ዕለት...
አዳፋ ነጠላ
በቀጠነ ገላ ÷ነፋስ የሚጥለው
የነተበ ጫማ
ጥቁር ያዘን ቀሚስ ÷ኑሮ ያጨቀየው
ለብሳ የተገኘች...
ከቤተክኪያን አጸድ ÷ቆማ ከዋርካ ስር
አንዲት ምስኪን ባልቴት...ትለማመን ነበር
አደራሽን ማርያም
አደራሽን ማርያም
እበላው የለኝ መሶቤ ተራቁቷል
እለብሰው የለኝም ጆርባየ በርዶታል።
ወድቃ እየተነሳች
እምባ እያፈሰሰች
ተስፋዋ ማርያምን ትለምናት ነበር
ከቤተስኪያን ጓሮ ቆማ ከዋርካ ስር።
•

የደብሩ አለቃ
ካባ ላንቃ ለብሶ  ሞጣህቱን ደርቦ
ልክ የሌለው ቦርጩ ወደፊት ተስቦ
የንግሡን ምእመን ወደፊቱ ስቦ
ጮክ ብሎ ያወራል
ጮክ ብሎ ያስተምራል።
፩
የመቅደሱ ቀለም ሊታደስ ይገባል
፪
የካህናት ደመወዝ ሊጨመር ግድ ይላል
፫
ደጀሰላም ወንበር እጅጉን ያንሰናል...
እናም...
በዚህ ታላቅ ደብር ይህ ችግር ስላለ
ለማርያም የሚሆን እጃችሁ የት-አለ?
እያለ።....

Scanned by CamScanner

## ብሩሽ ክንፎ ሲሆን

እንደ ረጉ ወንዞች.... እንደ ረጉ ሌቶች
ድምፅ እንደሌላቸው
ጎርፍ እንደሌላቸው.....
ከወፍ አረማመድ እግሩ ማይሠማ
አራት መስመር ቃሉ ዘለአለም ሚያደማ
ዘለአለም ሚሠማ...
ሊባኖስ ዝግባ ስር
በርሳስ የሚያሠምር
ከሴቶች ልቦና ሐረግ የሚፈጥር
ካገሩ ተሠዶ
ከራሥ ወንዙ ወርዶ
ለባዕዳን መሬት ብርሃን የሆናት
ጂብራን
ካህሊል ጂብራን
ስዕሉ ጨረቃ ግጥሞቹ ፀሐይ
ፊደሎቹ ኮከብ የርሱ ልብ ሠማይ
በርሳስ በብሩሹ ዓለምን የዞረ
እንደ-ሠው የሚኖር መልአክ የነበረ
ከንፉን ቃላት መሃል ዘርግቶ የኖረ
የዝምታ ድምፁ ካ'በቦች ያማረ
የሥዕሉ ቀለም ሽቱን ያሳፈረ
ጂብራን...
ካህሊል ጂብራን አንድ ሰው ነበረ፡፡
...
ይህ ሰው መልአክ ነበር
በሕይወት 'ሕዋ' ላይ በፊደል የሚኖር
በሐሣብ የሚሠክር፡፡
እናም ለዚህ ፍጥረት
ለርሱ ፊደል ማለት
ለርሱ ሥዕል ማለት....
ፊልሙንጢ የሚባል የራማ ድምፅ ነው
በመራራ ሕይወት....
ጥበብ ሲፈልጉ
ከሚኖሩ ሰዎች እግዜር የሚቀዳው፡፡...
አዎን ይሄ ፍጥረት
ያልፋል ሠማያቱን
ይገፋል ደመናን
ይገልባል ብርሃንን
ጂብራን ካሕሊል... ጂብራን....
(ደግሞም ሌላ ጊዜ)
ፍጥረት ሲመረምር ይጠልቃል ከባህር
ውበትን ሊሠፍር፡፡
ደግሞም ከሜዳ ላይ አበቦችን ያያል
ከንብ ትጋት ይልቅ.. እርሡ ቃል ይቀስማል
ወረቀት ቀፎው ላይ ፊደል ማር ያኖራል
ካህሊል ጂብራን ...ካህሊል፡፡
...
ይህ ሰው ሰው አይደለም
ከሠማይ መላዕክት አንዳ'ንዱ ነበረ
ቤአካለ ሥጋ ከእግዜር ቤት ርቆ...
በሲጋራው ዕጣን በቡና ጠበሉ ሲቀድስ የኖረ
ጂብራን መልአክ ነበር
ውሃ ላይ በንፋስ ስሙን ያሠፈረ፡፡
ነበር ያልነበረ፡፡
...
እናም ይህ ግዙፍ ሰው...
የብቻነት ሥቃይ ለራሱ ሣያንሰው
የዕልፍ ሰው ሐዘን ነው... ትከሻው የቻለው...
...
ቤቱን በሸፈነው በሲጋራው ዕጣን...
ከቤቱ ተቀምጦ ከመቅደስ ይገባል
አሁን እግዚአብሔር...
እንዲህ አይነት ካህን ቅድስት ውስጥ ያገኛል
ጂብራን በምናቡ....
ጴጥሮስን ይሆናል
ቶማስን ይሆናል
ይሁዳን ይሆናል
ስለሌሎች በደል ራሡን ይወቅሳል

ህዝቡን ያስተምራል
ህዝቡን ይደልላል፡፡..

ለንግሡ የመጡ...
ባለ ብዙ ብሮች
ብዙ ባለጠጎች...
ጥለት የለበሱ፥ በሽቶ የራሱ
ቆመው የነበሩ...እፊት ከመቅደሱ
ቀለም እንዲቀባ እንዲታደስ ደብሩ
ለደጀ ሰላሙ ደግሞም ለወንበሩ
በሺ.. 'የሚቆጠሩ
ብሮች ወረወሩ"...

የደብሩ አለቃ ግንባር በጣም ወዛ
የሚወረወረው ብሩም በጣም በዛ፡፡
•

የዛች የምስኪን ነፍስ
ያች ታላቅ መቅደስ
ቆማ ከዋርካ ስር
ተስፋዋ ማርያምን ትለማመን ነበር
አደራሽን ማርያም
አደራሽን ማርያም
እበላው የለኝም መሶቤ ተራቁቷል
እጠጣው የለኝም ማድጋዬ ጎድሏል
እለብሰው የለኝም ጀርባዬን በርዶታል
አንቺው ነሽ 'ተስፋዬ'፥ የኔ 'ተስፋ' ሞቷል
ወድቃ እየተነሳች
እምባ እያፈሰሰች፡፡
ግና-ግን ለዛሬ ፥ለክብርሽ እንዲሆን
ተቀበይ ስጦታ ውሰጂ እምሃዬን
የሟች ባሌን ማስታወሻ የአንገት ሃብሌን፡፡

•ለአብደላ ዕዝራ
ተበረከተ

## የእግዜር ሆድ ዥንጉርጉር ነዉ?

አብደላ ዕዝራ

ይህን "የማርያም ንግስ ዕለት" ግጥም፣ እስተ... የቤተክህነት አባት በዝግታ አንብበዉት፣ ለግለሰብ ስቃ... ሀሊናቸዉ ካቃሰተ አይደንቅም! ቅኔዉ እንቅልፍ የሚነሳ እቅ... ሸሽጓልና፡፡ የሰዉ ማንነት ሲገጣጠቡ፣ እንግልት ነፍስ... ሲጉረጉረዉ ፣ ግለሰብ ገመናዉን ተሸክሞ፣ የተስፋን ነጠብጣብ... ለመቃረም ከቤተክርስትያን ሲዳክር ዋይታዉን የተገነዘበ ካህ... ምላሹ ምን ይሆን?

> እበላዉ የለኝም መሶቤ ተራቁቷል
> እጠጣዉ የለኝም ማድጋዬ ጉድሏል
> እለብሰዉ የለኝም ጀርባዬን በርዶታል
> አንቺዉ ነሽ ተስፋዬ፣ የኔ ተስፋ ሞቷል

ገጣሚዉ ከሕይወት እንቅስቃሴ ጥቂት ትዕይንቶች - ያጣች የነጣች ባልቴት፣ የድብሩ አለቃ እና ብዙ ባለጠጉች -በመነጠል ስመመናዊ የብርሃንና የዕልመት ፊልም ይደቅንብናል፡፡ ግጥም ስሜትን ለማናኳት፣ በሆነ ጉዳይ ለመብሰክሰኩ በጨበት ለመደመም፣ ቢቀር ቢቀር በቋንቋዉ ንዝረት ለማገገም ይነበባል፡፡ አንብበነዉ እዉስጣችን እሚፈነዱ ለንዴት አሳልፎ እሚሰጠን ለባይተዋር ነፍስ ሆነ ለሌላዉ ጉዳይ እንድንቆረቆር፣ ከሀሊናችን እሚላወሰዉ በጣም በጣም ጥቂት ነዉ፡፡ ኪነጠቡቱ ሳይቀዝዙ ከልቦናችን ሳይደክም የሚኖር ከትኔ የመጠቀ ስንኝ የሚርመሰመስበት "የማርያም ንግስ ዕለት" ብርቅ ነዉ፡፡ የደበበ ሰይፉ የሚመጥኑት ሶስት ግጥሞች ትዝ ይሉኛል፡፡ የደበበ ሰይፉ "የንፋግ ምጽዋት" [የብርሃን ፍቅር፣ ገፅ 41-42] አንዱ ነዉ፡፡ የግጥሙ ተናጋሪ --ደበበም ሊሆን ይችላል--

ልብሱ እንደ ኑሮዉ የነተበበት ገበሬ በእጦት የቆሸሸች ሚስቱን አስከትሎ ከአቶቡስ ሲገባ፥ ገጣሚዉ ያስተዋለዉ ሁነትና የተሳፋሪዉ ምላሽ ይሰቀጥጣል።

ኮት ብለህ ዕድፍ ደርበህ፤
በገራ እጅህ ከዘራህን
በቀኝህ የልጆችህን እናት ጨብጠህ፥
ገባ ስትል "ወንድምዬ" የሴሳዉ ዐይንኮ ገሳመጠህ!

.......................................................

ከፊቷ አንገቷ ጠቁሮ፥ ደረቷ ጠቁሮ
እግሯ በንቅቃት ተቦርቡሮ፥ ተሸርሽሮ
ቦብሊን ሸንሸን ሰብሳ
በሳዩ ዶቃ ነገር፥ ጨሴ አፍሳ
ጸጉሯን በቅቤ አርሳ
ጨጨዋን እንደ ጨበጠች፥ የት ትቀመጠ፥ የት ታኖራት?
እንደ ሳስቲክ እየሰፋ ቦታዉን አጠበቡባት።
በልብሷ ተጠየፏት።
በጠረኗ ተሰቀቋት።
እስቲ በል፥ ደህችን እናት
የሀገር እናት የት ታኖራት?
[1965፥ ለታሪክ ፈሰግ ለሆኑ ወገኖቼ የተበረከተ]

ዮሐንስ አድማሱ 1965 የተቀኘዉ *"የደንገጎዋ ቆቱ"* [እስኪ ተጠየቁ ፥ገፅ 126 ] ኑሮ እያፈተለከባት፥ ልጇን በጀርባዋ አዝላ፥ ገበያ ለገበያ የምትባዝን እናት እራሷን እስከ ማደንዘዝ መባከኗ የተጤነበት ግጥም ነዉ። እንዲሁም 1958 በአፍላ እድሜዉ [ገፅ 97 - 98] *"የዋሁ ገበሬ"* በማለት የተቆጨበትን ግጥም ተቀኝቷል። ይህ አርሶ አደር ቤተክርስትያን ሳያስተጓጉል የሚመላለስ ፥ ነፍሱ የሰማዩን መንግሥት እንድትወርስ እያለመ፥ ምድር ላይ በድህነት መደፍጠጡ ያማል።

Scanned by CamScanner

ጠጠር ኩርንችቱ
እየቆረቆረዉ፥ እግሩን እየወጋ፥
ማስዳ ወደ ቆሳ፥
ማታ ወደ ደጋ።
ሕይወት የያዘችዉ በወሰድ አገድ፥
ሲወጣ ሲወርድ፥
ከሩቅ እየዋለሁ ሲወጣ ከቤቱ ከጉጆዉ ደሳሳ፥
ሲወጣ አቀርቅሮ፥
ዓይኑን መሬት ተክሎ፥
ነፍሱን ተሸክሞ ይዞ የወሳንሳ።

ከዮሐንስና ከደበበ የተጠቀሱት ግጥሞች ግለሰብ እንቅስቃሴ ላይ፥ ሳለ ለዕለት ጉርስ ሲባዝን ነው የተጤነበት። ኤፍሬም በግጥሙ የባልቴቷን ዱካ ብቻ ተከትሎ አልቀረፃትም። እዚያዉ ከአጠገቧ ለማርያም ንግስ ከረጢቱን የሚለጥጥ አለቃ፥ የተረፈዉም ባለፀጋ ሲመፃደቅ፥ ባልቴቷ ግን --ተስፋ ለመቁረጥ አንድ ስንዝር የቀራት-- በእልህ ስትለበለብ ንፅፅራዊ አያምነት ግጥሙን ጥልቀት ለገሰዉ። የእንቅስቃሴ ምት ወደ አራት አቅጣጫ ይሰነጣጠቅና ወደ እምብርቱ -የግለሰብ እንግልት- ይሰበሰባል። አንድ፥ ባሌቴቷ ወድቃ ትነሳለች፤ እመቤታችንን እየተለማመጠች። ሁለት፥ የደብር አለቃ አሽብርቆ በእጦት ለምትሰቃይ ነፍስ ሳይሆን፥ ለቤተክህነት ቁስ እና ቁሳቁስ ምእምናኑን ይማጠናል። ሶስት፥ ሽቶ እና ድሎት ያደመቃቸዉ ባለፀጐች ድህነት ጨረማምቶ፥ ከጉናቸዉ የጣላትን ልብስና ገላዋ ያለቀባት እንስት አትታያቸዉም *-invisible-* የሌለች ናት ለነሱ። *Sometimes the heart sees what is invisible to the eye* ይባላል። ስብአዊነት እዉስጣችን ከተላወሰ፥ አንዳንድ ጊዜ ለዐይን የተጋረደብን ለልቦናችን ፍንትዉ ብሎ ይገለጣል። አራተኛዉ አቅጣጫ ብትሸጠዉ ምናልባት አንድ ቀን፥ አንድ ሳምንት በህይወት የሚያቆያትን የሚች ባሏን ማስታወሻ ሀብል ከነፍሷ፥ ከትዝታዋ መንጥቃ ለእመቤታችን ክብር ትገብራለች።

Scanned by CamScanner

--------- ተፈጸመ ---------

Scanned by CamScanner



## የገጣሚው ቀደምት ሥራዎች

- “ሶልያና” ግጥምና ሙዚቃን በማዋሃድ የተሰራ አልበም 1998 ዓ.ም
- “ሙዚቃል” (የብርሃን ክንፎች) ሙዚቃና ግጥምን በማዋሃድ የተሰራ (Experimental) አልበም 2004 ዓ.ም
- “ፍቅር እዚህ ቦታ ፈገግ ብሉ ነበር” የግጥም መድብል 2005 ዓ.ም
- “ተዋናይ” ብሉይ የግዕዝ ቅኔያት ትርጓሜ ፍልስፍና 2006 ዓ.ም
- “የይሁዳ ድልድይ እና ሌሎች ሃሳቦች” የወግ ስብስብ 2007 ዓ.ም
- “ግጥም በመሰንቆ” (ከሌሎች ገጣሚያን ጋር) 2007 ዓ.ም

የሚዳሰስ ምርጊት ብቻ ሳይሆን ሥነልቦናዊ የትውልድ ብሶትና እልልታ ሸሽጓል ግድግዳው። እውቁ ሳይንቲስት አይሳክ ኒውተን አጭር ጥቅስ አለው። “We build too many walls and not enough bridges.” **ኤፍሬም** ከቀዳሚ አባቶች የተረከብነው ጣራና ግድግዳ በፍቅርም በጥበብም ድልድይ ጭምር መወከሉን ተቀኘበት።

**ሃያሲ አብደላ ዕዝራ**



Scanned by CamScanner